# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ | 84ኛ ዓመት | ቁጥር 036 | ጥቅምት 6 ቀን 2017 ዓ.ም | ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# "በአፍሪካ ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን ለመፍታት በአንድነት መቆም ይገባል"

- አቶ ተመስገን ጥሩነህ
የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር


ፎቶ ሔዳን አብርሃ

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ:- በአፍሪካ ያጋጠሙ የፀጥታን ችግሮችንና የተለያዩ ተግዳሮቶችን ለመፍታት ሌሎችን ከመመልከት ይልቅ በአሕጉሪቷ ያሉ አካላት በአንድነት መቆም ይገባቸዋል ሲሉ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ተመስገን ጥሩነህ ጥሪ አቀረቡ።

የአፍሪካ መከላከያ ሚኒስትሮች ጉባኤ "አፍሪካ በጠንካራ አንድነት፣ ለሁለንተናዊ ፀጥታና ሠላም" በሚል መሪ ሀሳብ ትናንትና በዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም መካሄድ ጀምሯል።

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ መድረኩን ሲከፍቱ ባደረጉት ንግግር፤ በአፍሪካ በአሁኑ ወቅት የፀጥታ ጉዳዮች፣ የውስጥ ግጭቶች፣ ድንበር ዘለል ግጭቶች፣ የሽብርተኝነትና የአክራሪዎች ስጋቶች እየጨመሩ መምጣታቸውን አንስተዋል።

ተግዳሮቶቹን ለመፍታት ወደ ሌሎች አካባቢዎች ማማተር ሳይሆን ለአፍሪካዊ ችግሮች አፍሪካዊ መፍትሔ በሚለው መርሕ መሠረት በጋራ መቆም እንደሚገባ አመላክተዋል።

አፍሪካውያን ለደኅንነታቸውና ለመፃኢ ዕድላቸው ኃላፊነት የሚወስዱበት ጊዜ ላይ መሆናቸውን የተናገሩት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ በአሕጉሪቱ እያጋጠሙ ያሉ ችግሮችን አስከፊነት በመገንዘብ ከመወያየት በዘለለ በንቃት ዘላቂ መፍትሔ ወደመፈለግ መሸጋገር እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል።

«በአፍሪካ ያጋጠሙ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








## ለሀገር ክብር በአንድነት የተሰለፉ ወንድማማቾች

ገጽ 2

# በክልሉ 14 ሚሊዮን ኩንታል የሩዝ ምርት ይጠበቃል

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል ከለማው መሬት 14 ሚሊዮን ኩንታል የሩዝ ምርት እንደሚጠበቅ የክልሉ ግብርና ቢሮ ገለጸ።

በአማራ ክልል ግብርና ቢሮ የሰብል ልማት ባለሙያ ወይዘሮ እንዬ አሰፋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በክልሉ በሩዝ ሰብል የሚሸፈነው ማሳ እንዲሁም የሚሰበሰበው ምርት ከዓመት ዓመት እየጨመረ መጥቷል።

የ2016/2017 ዓ.ም የምርት ዘመን በክልሉ 270 ሺህ 910 ሄክታር መሬት በሩዝ ሰብል ለመሸፈን ታቅዶ 150 ሺህ 225 ሄክታር መሬት ላይ ሩዝ እየለማ ይገኛል ብለዋል።

በተያዘው ዓመት በሩዝ ምርት ከተሸፈነው ማሳ 14 ሚሊየን ኩንታል ምርት ይገኛል ተብሎ እንደሚጠበቅ ባለሙያዋ አስታውቀዋል።

የማሳ ሽፋኑ ባደገ ቁጥር የምርት መጠኑ የሚጨምር በመሆኑ ክልሉ ምርት እንዲጨምር የማሳ ሽፋኑን ለማሳደግ በትኩረት እየሠራ መሆኑንም አመላክተዋል።

በምርታማነትም በሄክታር 49 ኩንታል ይገኝ ነበር አሁን ላይ እያደገ መጥቶ በሄክታር 53 ነጥብ ሦስት የኩንታል ሩዝ ምርት ይገኛል ተብሎ እንደሚጠበቅ ተናግረዋል።

እንደ ወይዘሮ እንዬ ገለጻ፤ የሩዝ ምርት ከዓመት ወደ ዓመት እየጨመረ የመጣበት ምክንያት ክልሉ ሩዝ ማምረት የሚችሉ አካባቢዎችን ወደ ማምረት እንዲገቡ ትኩረት ሰጥቶ በመደገፉ ነው ።

ሩዝ ማምረት እየቻሉ ወደ ምርት ያልገቡ አካባቢዎችን ለይቶ ድጋፍ በማድረግ፣ ሥልጠናዎችን በመስጠት እና በተወሰነ መልኩ ክልሉ ዘር በማቅረብ እንዲሁም አምራቾች ዘር እየተገበያዩ እንዲጠቀሙ በማመቻቸት ጠንካራ ሥራ መከናወኑን ገልጸዋል።

በአብዛኛው የሩዝ ማሳ በክላስተር እንደሚለማ የተናገሩት ባለሙያዋ፤ በአጠቃላይ በዘንድሮው የምርት ዘመን በሩዝ ምርት ከተሸፈነው ማሳ 115 ሺህ ሄክታሩ በክላስተር የሚለማ መሆኑንም ጠቁመዋል።

በክልሉ 14 ሚሊዮን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## ሞቼ የኢንቨስትመንት ከባቢን የመፍጠር እንቅስቃሴ

ገጽ 4



# ለሀገር ክብር በአንድነት የተሰለፉ ወንድማማቾች

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

**ዜና ሐተታ**

ሀገር ወዳድ ዜጎች በተልዕኮዋቸውና ሀገራቸውን በሚወዱት መጠን መስዋዕትነትን ይከፍላሉ። የሀገር ወዳድነት ፍቅር ሲታሰብ የሚከፈለው መስዋዕትነት ከሕሊና በላይ ሊሆን ይችላል። ወታደር በደምና በአጥንት የሕይወት መስዋዕትነት ለእናት ሀገሩ የመክፈል ዕድልን በተግባር የሚተረጉም ነው። ለዚህም ይመስላል ውትድርና የሀገር ወዳድነት ሚዛን ልኬቱ እንደሆነ ብዙኃኑ የሚናገሩት።

ወታደር ልክ እንደ ኃይለኛ ጅረት ነው ይባላል። ጅረት ኃይሉ ተዳክሞ እስኪረጋ ድረስ ተምዘግዝጊ ሆኖ እንደሚወርድ ሁሉ ወታደርም በነፍሱ ተወራርዶ የሕይወቱ ምዕራፍ እስኪከደን ገድሉን ከመፈጸም ወደ ኋላ አይልም። ይህ ገድል በሀገር ፍቅር ስሜት ሲታጀብ ደግሞ ሌሎችን ለማነሳሳትም የሀገር ሉዓላዊነትን ለማስጠበቅም ጠቃሚ ይሆናል።

የሀገር ፍቅር ስሜት ይነስ ይብዛ እንጂ በበርካታ ዜጎች ውስጥ የሚናወጥ የስሜት ማዕበል ነው። ይህን የሀገር ፍቅር ስሜት ደግሞ በደም ጭምር ለመክፈል የሚታደሉ በርካቶች ናቸው። በተለይ ከአንድ ማህፀን ወጥተው ለአንድ ዓላማ የሚሰለፉ ወጣቶች። ለዚህ ክብር የበቁ ጥቂቶች አክሊሉ አበራ እና ቴዎድሮስ አበራ ወንድማማቾች፤ ታላቅና ታናሽ የአንድ ማህፀን ተጋሪዎችም ናቸው።

ትውልድና እድገታቸው ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ ዞን ነው። ተነጣጥለው አያውቁም ውሎና አዳራቸውም አንድ ላይ ነው። ከቤተሰቦቻቸው የሚሰጣቸው ሥራ በጋራ ሲከውኑ፤ ሲተጋገዙ ቤተሰብ ሲረዱ እየተመረቁ አድገዋል።

እናት አባታቸውን በጋራ ከማገልገል የሀገርን ዳር ድንበር እስከመጠበቅ የዘለቀ ጥብቅ ቁርኝት አላቸው። እቅዳቸውና ተልዕኳቸው ሳይዛነፍ ብዙ የሕይወት ምዕራፎች ተራምደዋል።



ፎቶ፡- በረሀኑ ታደሰ

"እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ" እንዲሉ ሀገርን በደምና በላብ የማገልገል ውጥናቸውም በጋራ ያሰቡት ነው። ይህም ውጥን ከግብ ለማድረስ ጦላይ ወታደራዊ ማሠልጠኛ ትምህርት ቤት ገብተው እያንዳንዷን ሥልጠና በአግባቡ ተከታትለዋል።

ወንድማማቾቹ አክሊሉና አበራ የጦላይ ከፍተኛ ባለሌላ ማዕረግተኛ ወታደራዊ ማሠልጠኛ ትምህርት ቤት በመሠረታዊ ውትድርና በቅርቡ ካስመረቃቸው ምሩቃን መካከል ናቸው።

አሁን ደግሞ ለልዩ ተልዕኮና የሀገራቸውን ዳር ድንበር በመጠበቅ ለሉዓላዊነቷን ለማጽናት ተዘጋጅተዋል። አክሊሉና አበራ እንደማንኛውም ሰው የሃሳብ ልዩነቶች አሏቸው፤ ነገር ግን ሁሌም በሃሳብ የበላይነት የሚያምኑና ለጋራ ዓላማቸው ቅድሚያ የሚሰጡ በመሆናቸው ከዓላማቸው ጽናት ፈቀቅ ማለትን አይወዱም።

ወንድማማቾቹ እስከ መጨረሻዋ እስትንፋሳቸው እናት ሀገራቸው ለማገልገል ዛሬም እንደ ትናንቱ በአንድ ልብ በመምከር ቁርጠኛ መሆናቸው ይናገራሉ።

አክሊሉ አበራ ታላቅ ወንድም ሲሆን ከታናሽ ወንድሙ ቴዎድሮስ ጋር ከተወያየ በኋላ በውትድርና ሙያ ኢትዮጵያ ለማገልገል ወደ ውትድርና ሥልጠና መግባታቸውን ያስታውሳል።

ከልጅነቴ ጀምሮ መከላከያ ሠራዊት የመቀላቀል ከፍተኛ ፍላጎት ነበረኝ የሚለው መሠረታዊ ወታደር አክሊሉ፤ ከየትኛውም ዓይነት ወገንና ፓርቲ ድጋፍም ሆነ ተቃርኖም ሳይኖራቸው ሀገራቸው ብቻ ለማገልገል ወስነው ከቤት መውጣታቸውን ያብራራል።

በዚህም መሠረት ለራሳቸው በገቡት ቃልና በሥልጠናው ባገኙት ሀገራዊ እሳቤ በፍትሐዊነትና በታማኝነት ሀገራቸውን ያለ ልዩነት ለማገልገል ቁርጠኛ እንደሆኑም ያክላል።

ሥልጠናውም በሚገባ ተከታትለን መሠረታዊ ወታደር መሆን ችለናል፤ የሚሰጠንን ሀገራዊ ግዳጅ በአግባቡ ለመወጣት ዝግጁ ነው ሲል ሃሳቡን ይገልጻል።

ሀገሪቷን ከውጭ ወራሪና ከውስጥ ፀረ-ሠላም ኃይል ለመጠበቅ እንዲሁም ዘላቂ ልማት እንዲረጋገጥና የኢኮኖሚ አውታሮቿ ሠላማዊ እንቅስቃሴ እንዲኖራቸው ለማድረግ ወንድማማቾቹ ዝግጁ ናቸው።

መሠረታዊ ወታደር ቴዎድሮስ አበራ በበኩሉ፤ ከታላቅ ወንድሙ ጋር ሠልጥኖ ወታደር ለመሆን በመብቃቱ ደስተኛ መሆኑን ይናገራል።

በበፊት ሕይወታችንም ተነጣጥለን አናውቅም፤ በሥራ አጋጣሚ የትም ስንሄድ አብረን ነው የምንሄደው የሚለው መሠረታዊ ወታደር ቴዎድሮስ፤ አሁንም በሥልጠና ባገኘነው እውቀትና ብሔራዊ እሳቤ በጋራ ለመሥራት ዕድሉን አግኝተናል ይላል።

መሠረታዊ ወታደር ቴዎድሮስ፤ በማዕከሉ በርካታ የተግባርና የንድፈ ሃሳብ ሥልጠናዎች ማግኘታቸውን ጠቅሶ፤ በውትድርና ሙያ ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነት መስዋዕት ለመክፈል ዝግጁ ነኝ፤ ማንም ሀገሬን ላይ ጉዳት እንዳያደርስ እኔ ቀድሞ እደርስላታለሁ ሲል ለውትድርና ሙያ ያለውን ክብርና ለሀገሩ ያለውን ፍቅር ይገልጻል።

ወንድማማቾቹ ከቤተሰብ ጀምሮ ያላቸውን ጥብቅ ቁርኝት በማስፋት በሠራዊቱ ውስጥ ለአንድ ዓላማ የመሰለፍን ሙያዊ ግዴታ በመላበስ ሀገርን ለማገልገል ዝግጁ መሆናቸውን ወኔ በተሞላበት ስሜት አስረድተዋል።

# ሀገራዊ ምክክሩ - ጠንካራ ኢትዮጵያን ለመገንባት

**ተስፋ ፈሩ**

**ዜና ሐተታ**

ሀገራዊ ምክክሩ የአጀንዳ ማሰባሰብ ምዕራፍ በተለያዩ ክልሎች እየተካሄደ ይገኛል። የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን በአፋር ክልል በቅርቡ የአጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር ምዕራፍን ማጠናቀቁ ይታወሳል። በአሁኑ ወቅት ደግሞ በሶማሌ ክልል የአጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር ምዕራፍን እየተከናወነ ይገኛል።

ምክክሩ አንድነቷ የተጠበቀ ጠንካራ ኢትዮጵያን ለመገንባት የሚያስችል ሂደት መሆኑን በርካታ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚገልጹት ጉዳይ ነው። በሂደቱ የተሳተፉ በክልሉ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተወካዮች ሀገራዊ ምክክሩ አንድነቷ የተጠበቀ ጠንካራ ኢትዮጵያን ለመገንባት ያስችላል የሚል እምነት እንዳላቸው ለኢፕድ ተናግረዋል።

የአፋር አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር ምክትል ሊቀመንበር መሐመድ አወል፤ እንደ ፓርቲ የሀገራዊ ምክክሩን አስፈላጊነትን ለረጅም ጊዜ ስናነሳው የነበረ ጉዳይ ነው። የረጅም ጊዜ ጥያቄያችን በለውጡ መንግሥት ምላሽ በማግኘቱ የራሳችንን ዝግጅት በማድረግ የምክክር ሂደቱ የሚጀመርበትን ጊዜ በጉጉት ስንጠብቅ ቆይተናል ይላል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ ሆኖ ጠንካራ ኢትዮጵያን መመሥረት እንዲችል ትርክቶቻችን ሊመሳሰሉ ይገባል በሚል ውይይቱን መጠበቃቸውን የሚጠቁሙት ምክትል ሊቀመንበሩ፤ የምክክር መድረኩ ሲከፈት ፓርቲያቸው በራሱ በኩል በጉባዔ ደረጃ ተነጋግሮበት ዝግጅት አድርጎ የለያቸውን አጀንዳዎች ይዞ መቅረቡን ያስረዳሉ።

አቶ መሐመድ እንደሚያስረዱት፤ ሀገራዊ ምክክር ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት አንድነታችንን ጠብቀን ጠንካራ ኢትዮጵያን ለመገንባት ነው። ምክክሩ ከሁሉም የኅብረተሰብ ክፍሎች የወጡ አካላት ተገናኝተው በሠለጠነ መንገድ ተነጋግረው ለሀገርና ለወገን የሚበጅ ስምምነት ላይ እንዲደርሱ ያደርጋል።

ፓርቲያቸው ጠንካራ ኢትዮጵያን ለመመሥረት እንደሚሠራ ያመላከቱት ምክትል ሊቀመንበሩ፤ በዚህ ውይይት አናምንም ብለው የቀሩ ፓርቲዎች ጥርጣሬያቸውን ወደጎን በማራቅ ችግሮች የሚፈቱት ተቀራርቦ በመነጋገር ስለሆነ ወደ ምክክሩ ሊመጡ ይገባል ይላሉ።

የአፋር ነፃ አውጪ ግንባር የፓርቲ ሥራ አስፈጻሚ አባል አሕመድ ሐሰን በበኩላቸው፤ ሀገራዊ ምክክሩ እንደ ክልል ለአፋር ሕዝብ እንደ ሀገር ደግሞ ለመላው ኢትዮጵያውያን ጠቃሚ መሆኑ ነው የተናገሩት።

በተለይም በአሁኑ ሰዓት ያሉትን ችግሮች በማስወገድ ሀገራችንን ከመበታተን አደጋ ታድጎ ሕዝባችን ተፈቃቅሮ በአንድ እንዲኖር ያደርጋል ሲሉ ያስረዳሉ።

ሠላም መምጣት የሚችለው በሰከነ መንገድ ዴሞክራሲያዊ ውይይት አድርጎ መግባባት ሲቻል ነው። ምክክሩ የሀገራችን ችግር የት ላይ ነው የሚለውን ለይቶ ቁስሏን እንዴት ማከም እንደሚቻል የሚያመላክትና ያለፉ ሥርዓቶች የፈጠሯቸው ጠባሳዎች ዳግም እንዳይከሰቱ ትክክለኛ አቅጣጫ የሚያስቀምጥ ይሆናል ብለን እንጠብቃለን ይላሉ።

በአፋር ክልል የተደረገውን የአጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር ምዕራፍ ሂደት ፓርቲያቸው አሳታፊና ዴሞክራሲያዊ ሆኖ እንዳገኘው የጠቆሙት አሕመድ፤ እኛ የሀገራችንን የሕመም ምክንያት ነው የምንለውን ለይተንና መክረን አጀንዳችንን አስተላልፈናል ሲሉ ይናገራሉ። ይህም ከሌሎች ክልሎች ከሚሰበሰቡ አጀንዳዎች ጋር ተደምሮ ሀገራዊ ምክክር ተደርጎበት ሀገራችንን የሥልጣኔ ማማ ላይ ለማስቀምጥ የሚያስችል ጉዞ እንድናደርግ ያግዘናል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ ብለዋል።

የአርጎባ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ ፓርቲ አመራሩ ጀማል ሐሰን በበኩላቸው፤ ሀገራችንን ለማሳደግ እና ሠላም እንዲሰፍን ለማድረግ በሀገር ደረጃ ብቻ ሳይሆን ከወረዳ ጀምሮ ባሉት የአስተዳደር አወቃቀሮች የሚወከሉ የኅብረተሰብ ክፍሎች እና ባለድርሻ አካላት የሚሳተፉበት ምክክር ማካሄድ ያስፈልጋል ባይ ናቸው። አሁን የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን እያካሄደ የሚገኘው ይህን በጎ ተግባር በመሆኑ መደገፍ እንደሚገባ ይገልጻሉ።



ሀገራዊ ምክክሩ አሁን ያለውን ግጭት ምድራችን ሠላም እንዲሰፍን ያደርጋል ብለው እንደሚያምኑ የሚገልጹት የፓርቲ አመራሩ፤ በተያያዘው መንገድ ከተመካከርንና ከተወያየን ጥሩ ደረጃ ላይ ደርሰን ችግሮቻችንን እንፈታለን ሲሉ ይጠቁማሉ።

በአጠቃላይ የተጀመረው የምክክር ሂደት ጠንካራ ሀገር እንዲኖረንና ወደ ተሻለ ደረጃ ከፍ የምንልበትን ዕድል ይሰጣል የሚል ዕምነት እንዳላቸው ይናገራሉ።

ክልላችን በሀገራዊ ምክክሩ የሚያደርገው ተሳትፎ ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍሎችና ባለድርሻ አካላት ያካተተ እንዲሆን በቂ ዝግጅት ተደርጎበት የአጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር መድረኩ በጥሩ መንገድ ተከናውኗል ይላሉ።


በክልላችን የሚንቀሳቀሱ ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ብልፅግና ፓርቲም የራሳቸውን አጀንዳ አቅርበው ውይይትና ምክክር ተደርጎባቸዋል የሚሉት ደግሞ የአፋር ክልል ዞን አንድ ብልፅግና ፓርቲ ጽሕፈት ቤት ኃላፊው ናስር መሐመድ ናቸው።

ሀገራዊ ምክክሩ ከዚህ ቀደም ያልነበረ ለመጀመሪያ ጊዜ የተገኘ ዕድል መሆኑን የሚያወሱት የፓርቲው ጽሕፈት ቤት ኃላፊው፤ ቀደም ሲል ዜጎች ሀሳባቸውን በነፃነት የሚያስተናግዱበት መንገድ ሳይኖራቸው በመቅረቱ የተለያዩ ምርጫዎች ውስጥ የገቡበት ሁኔታ መኖሩን ያስታውሳሉ።

ምክክሩ ይዞ የመጣው የትኛውንም ሀሳብ በጠረጴዛ ዙሪያ መፍታት የሚቻልበትን አማራጭ ነው። ምክክሩ ገና የጅማሬ ሂደት ላይ የሚገኝ ቢሆንም እስካሁን እየታየ ያለው ሂደት የሚበረታታ ነው ይላሉ።

አያይዘውም፤ ሀገራዊ ምክክሩ ሕገመንግሥቱን ጨምሮ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ በተናጠልና በወል የሚነሱ ጥያቄዎች ላይ በስፋት ምክክር ተካሂዶባቸው በውይይት ሂደትና በሕዝብ ድምፅ መልስ የሚያገኙበት መሆኑን ይጠቁማሉ። ከምክክሩ በኋላ እንደ ሀገር ይዘን የምንጓዘው የጋራ ገዢ ሀሳብ እና ትርክት ይኖረናል የሚል እምነት አለን። በውጤቱም ሀገራችን እየተጓዘች በምትገኝበት የእድገት ጎዳና ላይ በፍጥነት እንድትገሰግስ በር ይከፈታል ሲሉ ሀሳባቸውን ቋጭተዋል።

ዜና



## የሕንፃ ግንባታዎች የመሬት መንቀጥቀጥን የሚቋቋሙ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይገባል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- ማንኛውም የሕንጻ ግንባታዎች ሲከናወኑ የመሬት መንቀጥቀጥን የሚቋቋሙ መሆናቸውን ማረጋገጥ እንደሚገባ በሰመራ ዩኒቨርሲቲ የፊዚክስ መምህሩ ፍሬወሊጋ ገለታ ገለጹ፡፡

መምህሩ ፍሬወሊጋ ገለታ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የሕንጻዎች ግንባታዎች ጂኦሎጂካል መረጃን መሠረት ያደረጉና የመሬት መንቀጥቀጥ ቢከሰት መቋቋም የሚችሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይገባል።

ሰሞኑን በአዋሽ ፈንታሌ አካባቢ ያጋጠመው የመሬት መንቀጥቀጥ ንዝረት አዲስ አበባ ድረስ መሰማቱን አስታውሰው፤ ኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ አካባቢዎች የመሬት መንቀጥቀጥ ድጋሚ ሊከሰት ስለሚችል ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባ አመላክተዋል።

ትላልቅ ሕንጻዎች በሚገነቡበት ወቅት ጂኦሎጂካል መረጃን መሠረት በማድረግ እንዲሁም የመሬት መንቀጥቀጥን መከላከል የሚያስችል አሠራርን ሊከተሉ እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

አስፈላጊው የአፈር ምርመራና ጥናት በማካሄድ የመሬት መንቀጥቀጥ ቢከሰት እንኳን ሊሰነጠቅ የማይችል ጠንካራ ሕንፃ መገንባት የሁልጊዜም ሥራ ሊሆን እንደሚገባ ጠቁመው፤ ከአካባቢው ሁኔታ ጋር የተዛመደና በጥናት ላይ የተመሠረተ ግንባታን በማካሄድ አደጋዎችን መቀነስ እንደሚያስፈልግ አመላክተዋል።

የመሬት መንቀጥቀጥ በአለቶች ግጭትና መላቀቅ፣ በእሳተ-ገሞራ ሂደት፣ በኬሚካልና ኒውክሌር ፍንዳታ እንዲሁም በሰው ሠራሽ መንገድ ሊከሰት እንደሚችል አስረድተዋል።

ከሰሞኑ የደረሰው የመሬት መንቀጥቀጥ በቀጣይም ሊከሰት ስለሚችል ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል ሲሉ አሳስበዋል። እንደ ፍሬወሊጋ ገለጻ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ በዚህ ጊዜ ይከሰታል ብሎ መገመት ባይቻልም ጥንቃቄ ማድረጉ ተገቢ ነው፡፡

በሰመራ ዩኒቨርሲቲ የተዋቀረ የጥናት ቡድን የመሬት መንቀጥቀጥ በተከሰተበት አካባቢ በመሄድ ምልከታ ማድረጋቸውን እና በቀጣይም ጥናትና ምርምር በማድረግ ለሚመለከተው ባለድርሻ አካላት ለማድረስ እንደሚሠራ ገልጸዋል፡፡

የአፋር ማኅበረሰብ ከቦታ ቦታ እየሄደ የሚኖር ማኅበረሰብ በመሆኑ ጉዳት እንዳይደርስባቸው የማስገንዘብ ሥራ እየተሠራ መሆኑን ጨምረው ተናግረዋል፡፡

የመሬት መንቀጥቀጥ በሚከሰትበት ወቅት ኅብረተሰቡ ፎቅ ላይ ካሉ ወደ ኮለን መጠጋት መሬት ላይ ከሆኑ ደግሞ ከኤሌክትሪክ ማማዎች በመራቅ እና ገላጣ አካባቢዎች በመሆን እራሳቸውን ሊጠብቁ እንደሚገባ አስረድተዋል፡፡

በአዋሽ ፈንታሌ አካባቢ መስከረም 26 ቀን 2016 ዓ.ም የተከሰተው የመሬት መንቀጥቀጥ በሬክተር ስኬል አራት ነጥብ ዘጠኝ ሲሆን ጥቅምት 3 ቀን 2017 የተከሰተው ደግሞ በሬክተር ስኬል አራት ነጥብ ስድስት ሆኖ መመዝገቡን አስታውሰዋል፡፡

የተከሰተው አደጋ የጉዳት መጠንም ዝቀተኛ ነው ያሉት ፍሬ ወሊጋ፤ በቀጣይ የከፋ ጉዳት እንዳይደርስ ምርምሮችን ማድረግ ይገባል ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ የስምጥ ሸለቆ መገኛ እንደመሆኗ የከፋ ጉዳት ባያደርስም በተለያዩ ጊዜያት የመሬት መንቀጥቀጥ አጋጥሟታል፡፡

በ1900 ዓ.ም ስድስት ነጥብ ሰባት፣ በ1909 ዓ.ም ስድስት ነጥብ ስምንት እንዲሁም በ1961 ዓ.ም ስድስት ነጥብ አምስት በሬክተር ስኬል የተመዘገበ የመሬት መንቀጥቀጥ መከሰቱን የጂኦሎጂ መረጃዎች ያሳያሉ።

# በክልሉ ለመኸር እርሻ 8 ነጥብ 7 ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ቀርቧል

- 11 ነጥብ 2 ሚሊዮን ሔክታር መሬት በዘር ተሸፍኗል
- 337 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይጠበቃል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- በ2016/17 የምርት ዘመን ለመኸር እርሻ ስምንት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ኩንታል የኬሚካል የአፈር ማዳበሪያ ማቅረቡን የኦሮሚያ ክልል ግብርና ቢሮ አስታወቀ። በዘር ከተሸፈነው 11 ነጥብ 2 ሚሊዮን ሔክታር መሬት 337 ሚሊዮን ኩንታል ምርት እንደሚጠበቅም ተገልጿል።

የቢሮው ኃላፊ አቶ ጌቱ ገመቹ ትላንት በሰጡት መግለጫ እንዳመላከቱት፤ በ2016/17 የምርት ዘመን ለመኸር እርሻ ስምንት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ኩንታል የኬሚካል አፈር ማዳበሪያ ማቅረብ ተችሏል።

እንደ አቶ ጌቱ ገለጻ፤ በተለያዩ ሰብሎች ከተሸፈነው 11 ነጥብ 2 ሚሊዮን ሄክታር መሬት 337 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይጠበቃል።

በዘር ከተሸፈነው መሬት ውስጥ ስምንት ሚሊዮን 651 ሺህ ሄክታር በኩታ ገጠም ማልማት ተችሏል ያሉት ኃላፊው፤ በአጠቃላይ በዘር ከተሸፈነው መሬት 78 በመቶውን በክላስተር የለማ መሆኑን አስታውቀዋል።

በምርት ዘመኑ የኬሚካል ማዳበሪያን፣ መደበኛና ቨርሚ ኮምፖስትን ለአርሶ አደሩ ማቅረብ መቻሉን ጠቅሰው፤ ለአርሶ አደሩ ከቀረበው ስምንት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ኩንታል የኬሚካል አፈር ማዳበሪያ ውስጥ ከስምንት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን በላይ ኩንታል ጥቅም ላይ መዋሉን ገልጸዋል።

በክልሉ የሜካናይዜሽን፣ የቴክኖሎጂ አጠቃቀምና የባለሙያዎች ምክር እያደገ መምጣቱን አንስተው፣ አራት ሚሊዮን ሔክታር መሬት በሜካናይዜሽን ታግዞ መልማቱን ተናግረዋል።



በበቆሎ ሰብል ልማት ሁለት ሚሊዮን ሔክታር መሬት በዘር መሸፈኑን የገለጹት አቶ ጌቱ፤ አንድ ሚሊዮን 40 ሺህ ሔክታር መሬት በማሽላ ሰብል ዘር እንደተሸፈነ ጠቁመዋል።

በመኸር እርሻ ሦስት ሚሊዮን 165 ሺህ ሄክታር መሬት በስንዴ ሰብል መሸፈኑን ጠቅሰው፤ ከውጪ የሚገባውን የቢራ ገብስ ለማስቀረት 528 ሺህ ሄክታር መሬት በዘር መሸፈኑን ገልጸዋል።

የሩዝ ምርትን ለማሳደግ አንድ ሚሊዮን 918 ሺህ ሔክታር መሬት መልማቱን አስረድተው፤ 603 ሺህ ሄክታር በአኩሪ አተር ፣ 518 ሺህ ሄክታር በለውዝ፣ 180 ሺህ ሄክታር መሬት ደግሞ በሱፍ ዘር መሸፈኑን አስረድተዋል።

ለውጪ ገበያ እንዲቀርቡ ከሚሠራባቸው ሰብሎች መካከል የቦሎቄ ምርት አንድ ሚሊዮን 81 ሺህ ሄክታር መሬት በዘር መሸፈኑን በመግለጽ፤ ሰሊጥ 500 ሺህ ሔክታርና ማሾ 300 ሺህ 112 ሄክታር መሬት ላይ መልማታቸውን ተናግረዋል።

በእንስሳት ልማት በሰው ሠራሽ ዘዴ አንድ ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ላሞችና ጊደሮችን ማዳቀል ተችሏል ያሉት ኃላፊው፤ 53 ሚሊዮን የአንድ ቀን የዶሮ ጫጩቶችን ለአርሶና ከፊል አርብቶአደሩ የማከፋፈል መቻሉን አስታውቀዋል።

በሌላ በኩል አንድ ሚሊዮን 31 ሺህ ዘመናዊ የንብ ቀፎዎችን ማከፋፈል መቻሉን ጠቁመዋል።

# የአደጋ ጊዜ ምላሽ የድጋፍ ፕሮጀክት ይፋ ሆነ

**ቃልኪዳን አሳዬ**




ፕሮጀክቱ ለሁለት ዓመታት ተግባራዊ ይደረጋል

አዲስ አበባ፡- የዓለም አቀፍ የገጠር መልሶ ግንባታ ኢንስቲትዩት (IIRR) በአዲስ አበባ ከተማ፣ በሲዳማ እና በደቡብ ኢትዮጵያ ክልሎች ተግባራዊ የሚደረግ የአደጋ ጊዜ ምላሽ አገልግሎት የልማት ድጋፍ ፕሮጀክት ይፋ አደረገ።

ፕሮጀክቱ ትናንትና ይፋ ሲደረግ የኢንስቲትዩቱ ካንትሪ ዳይሬክተር ዘሪሁን ለማ እንደገለፁት፤ ከፖላንድ መንግሥት በተገኘ ድጋፍ ከፖላንድ ዓለም አቀፍ እርዳታ ማዕከል (PCPM) ጋር በመተባበር ለሁለት ዓመታት ተግባራዊ የሚደረገው ፕሮጀክት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፣ በሲዳማና በደቡብ ኢትዮጵያ ክልሎች ይተገበራል።

ለፕሮጀክቱ ተግባራዊነት አንድ ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ዶላር መበጀቱን አስታውቀው፤ በመዲናዋ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እሳትና አደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን የእሳት አደጋ ተከላካዮችና የአምቡላንስ ባለሙያዎች ሥልጠና ለመስጠትና የአምቡላንስ ሠራተኞችን የቅድመ ሆስፒታል እንክብካቤ አቅም ለማሳደግ እንደሚሠራ አመላክተዋል።

በፕሮጀክቱ አማካኝነት ለእሳት አደጋ መከላከል የሚያገለግሉ መሣሪያዎች ድጋፍ እንደሚደረግ አንስተው፤ ፕሮጀክቱ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የሚገኙ የማኅበረሰብ አቀፍ የእንስሳት ጤና ባለሙያዎችን አቅም ለማሳደግ፣ ለአርብቶ አደር ማኅበረሰቦች የእንስሳት ጤና አጠባበቅ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ የሚያስችል መሆኑን ገልጸዋል።

የፖላንድ ዓለም አቀፍ ርዳታ ማዕከል ሥራ አስኪያጅ ዎጅቴክ ዊልክ (ዶ/ር) በበኩላቸው። ማዕከሉ በኢትዮጵያ ያለውን የአደጋ ስጋት መከላከል አቅምን ለማጠናከር ድጋፍ እያደረገ ነው ብለዋል።

በተጨማሪም የሰብዓዊ ርዳታ፣ የሕክምና ድጋፍና ለኢትዮጵያውያን ድንገተኛ የሕክምና ቡድን አባላት የአቅም ማጎልበቻ ድጋፍ እያደረገ መሆኑን ጠቅሰው፤ ማዕከሉ በኢትዮጵያ በነበረው የ12 ዓመታት ቆይታ ከአራት ነጥብ አራት ሚሊዮን ዶላር በላይ ወጪ በማድረግ በትምህርት፣ በጤናና በሌሎችም ዘርፎች 10 ፕሮጀክቶችን አጠናቆ ወደትግበራ ማስገባት መቻሉን ጠቁመዋል።

ፕሮጀክቱ ቀደም ሲል በኬንያ ተግባራዊ መደረጉን ያነሱት ሥራ አስኪያጁ፤ በኢትዮጵያ ለፕሮጀክቱ ተግባራዊነት ምቹ ሁኔታዎች አሉ ያሉት ዎጅቴክ (ዶ/ር)፤ በዚህም የአዲስ አበባ ከተማ እሳትና አደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን በቂ ሠራተኞችና የድንገተኛ እሳት አደጋን መከላከል የሚያስችሉ ማዕከላት መኖራቸውን ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ በቀጣናው ድንገተኛ አደጋዎችን ለመከላከል የሚያስችል ትልቅ ተቋም መገንባት መቻሏን በመግለጽ፤ ፕሮጀክቱ በዋነኝነት ለሙያተኞች የክህሎትና የቁሳቁስ ድጋፍ ለማድረግ የሚያስችል መሆኑንም አመላክተዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እሳትና አደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን የድንገተኛ አደጋዎች ሕክምናና አምቡላንስ አገልግሎት ዳይሬክተር ዑመር አብዱራዛቅ በበኩላቸው፤ ኮሚሽኑ በወሳኝ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በማድረግ የሪፎርም ሥራ በማከናወን ላይ ይገኛል ብለዋል።

የሠራተኞችን አቅም በማሳደግና ዘመናዊ መሣሪያዎችን በመጠቀም ረገድ ይህ ፕሮጀክት ኮሚሽኑ እያከናወነ ከሚገኘው ሥራ ጋር ከፍተኛ ቁርጠኝነት ያለው መሆኑንም ገልጸዋል።

ፕሮጀክቱ እንዲተገበር ላደረጉት አካላት ምስጋና ያቀረቡት አቶ ዑመር፤ ፕሮጀክቱ እስኪጠናቀቅ ኮሚሽኑ የበኩሉን አስተዋፅዖ ለማድረግ ዝግጁ መሆኑን አስገንዝበዋል።

# ምቹ የኢንቨስትመንት ከባቢን የመፍጠር እንቅስቃሴ

**ቃልኪዳን አሳዬ**

**ዜና ሐተታ**

ኢትዮጵያን ለሀገር ውስጥና ለውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት አልሚ ባለሀብቶች ተመራጭ ማድረግ ያስቻሉ የአዋጅ፣ የአሠራርና ሌሎችም በርካታ ማሻሻያዎች እንዲሁም የኢንዱስትሪ ፓርኮች ግንባታዎች ተከናውነዋል። በዚህም በየጊዜው የኢንቨስትመንት ፍሰቱ እያደገ በመምጣቱ ኢትዮጵያ ከምሥራቅ አፍሪካ ዋናዋ የኢንቨስትመንት መዳረሻ እየሆነች ነው።

እንደ ሀገር ለዘርፉ የተሰጠውን ልዩ ትኩረት ከሚመሰክሩ ሥራዎች አንዱ በኦሮሚያ ክልል ዱከም ከተማ የሚገኘው እ.አ.አ በ2007 የተቋቋመው የኢስተርን ኢንዱስትሪ ፓርክ ነው። ከሰሞኑ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የሥራ ኃላፊዎችና የመገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች የኢንዱስትሪ ፓርኩን የሥራ እንቅስቃሴ ተዘዋውረው ጎብኝተዋል።




ጉብኝቱ በፓርኩ የኢንቨስትመንት ዘርፍ ከተሠማሩት ከ153 በላይ የውጭ አልሚ ባለሀብቶች ይገኛሉ። በፓርኩ የሚገኙ ኩባንያዎች የምርት እንቅስቃሴና የሚደረግላቸው ድጋፍ ምን እንደሚመስል ለኢፕድ ሃሳባቸውን አጋርተዋል።

ሊንዳ ኢትዮጵያ ጋርመንት በኢስተርን ኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ከተሰማሩ የቻይና ኩባንያዎች መካከል አንዱ ነው። የኩባንያው ጀነራል ማናጀር ሚስተር ጄ ይፋን እንደሚገልጹት፤ በኢትዮጵያ ኢንቨስት በማድረጋቸው እጅግ ደስተኛ ናቸው። ሊንዳ ኢትዮጵያ እ.አ.አ በ2013 የተቋቋመ ሲሆን ለ10 ዓመታት ያህል የተለያዩ የአልባሳት ውጤቶችን በማምረት ለገበያ ሲያቀርብ ቆይቷል።

ኩባንያው በስሩ ከአንድ ሺህ በላይ ለሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል ፈጥሯል የሚሉት ሚስተር ጄ፤ ከዚህ ቀደም ብዛት ያላቸውን የተለያዩ አልባሳት በማምረት ወደአሜሪካና አውሮፓ ሀገራት ያቀርብ እንደነበር ነው የተናገሩት።

የተለያዩ የጨርቅ ግብዓቶች ከውጭ በማስገባት ተኪ ምርቶችን ለማምረት በተጀመረው እንቅስቃሴ ኩባንያው ምርቶቹን ለኢትዮጵያ ገበያ እያቀረበ ሲሆን መንግሥትም ተገቢውን ድጋፍ እያደረገልን ነው ይላሉ።

ሌላኛው በኢስተርን ኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ የተሠማራው የቻይና ኩባንያ እ.አ.አ በ2016 በ181 ሚሊዮን ብር ካፒታል የተቋቋመው ሁአጂያን አሉሚንየም ነው።

ከ170 በላይ ለሚሆኑ ኢትዮጵያውያን ሠራተኞች በቋሚነት የሥራ ዕድል ፈጥሯል። በተለያየ ዲዛይንና ቀለም ለበር፣ ለመስኮትና ለሌሎች አገልግሎቶች የሚውሉ 16 አይነት የአሉሚንየም ፕሮፋይሎችን በማምረት ለሀገር ውስጥ ገበያ እንደሚያቀርብ የኩባንያው ጀነራል ማናጀር ሚስተር ዴቪድ ዞሁ ይናገራሉ።

እንደ ጀነራል ማናጀሩ ገለጻ፤ ካምፓኒው በግብዓትነት የሚጠቀመው የአገልግሎት ጊዜያቸው ያበቁና የወዳደቁ አሉሚንየሞችን ሲሆን፣ እጥረት ሲኖርም ከውጭ ያስገባል።

ድርጅቱ በቀን ከ10 እስከ 15 ቶን በማምረት ለሀገር ውስጥ ገበያ እያቀረበ ቢሆንም ያለውን ፍላጎት ማሟላት ባለመቻሉ እና በቂ ግብዓት ባለማግኘቱ ለውጭ ገበያ ማቅረብ አዳጋች ሆኖበታል። ከውጭ ምንዛሪ እጥረትና ከግብዓት ጋር የተያያዙ ችግሮችም አሉበት ይላሉ።

የኢስተርን ኢንዱስትሪ ፓርክ ማኔጅመንት ኮሚቴ ሺያ ዞሁ በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያና ቻይና በርካታ ዓመታትን በዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት አሳልፈዋል።

በዚህም ከፓርኩ ምሥረታ ጀምሮ የኢትዮጵያ መንግሥት ተገቢውን ድጋፍ በማድረግ ላይ ይገኛል። ምቹ የሥራ ከባቢ በመፍጠሩ በፓርኩ የሚገኙ ኩባንያዎች በአግባቡ የምርት ሂደት በማከናወን ላይ ይገኛሉ ሲሉ ያስረዳሉ።

ፓርኩ የአካባቢውን ማኅበረሰብ ጨምሮ ከክልል፣ ከፌደራልና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ሁሉ በቅርበት እየሠራ ነው። በዚህም ምቹ የመሥሪያ ከባቢ መፍጠር ተችሏል። በፓርኩ የሚገኙ ካምፓኒዎች ቁጥርም እየጨመረ መምጣቱን ጠቅሰዋል።

የቻይናና የኢትዮጵያ ግንኙነት ከጊዜ ወደጊዜ በሁሉም ዘርፎች እያደገ መጥቷል፤ ኢትዮጵያ ባለፈው ዓመት የብሪክስ አባል መሆኗ የሁለቱን ሀገራት ግንኙነት በይበልጥ ለማሳደግ ምቹ አጋጣሚን ተፈጥሯል ይላሉ።

ሚስተር ሺያ ዞሁ እንዳመላከቱት፤ በቅርቡ ተግባራዊ የተደረገው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ የተለያዩ ግብዓቶችን ከውጭ በማስገባት በፓርኩ የሚገኙ ካምፓኒዎችን የማምረት አቅም ለማሳደግ ያግዛል። በዚህም በርካታ የሥራ ዕድሎችን በመፍጠር የአካባቢውን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ለማጠናከር ያግዛል።

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር ዘለቀ ተመስገን (ዶ/ር) እንደሚገልፁት፤ ለውጡን ተከትሎ ምቹ የኢንቨስትመንት ከባቢን በመፍጠር ኢትዮጵያን ለሀገር ውስጥና ለውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት አልሚ ባለሀብቶች ተመራጭ ለማድረግ በተሠሩ የሕግ፣ የኢኮኖሚና ሌሎችም በርካታ ማሻሻያዎች በየጊዜው ወደኢትዮጵያ ኢንቨስት ለማድረግ የሚመጡ ባለሀብቶች ቁጥር ጨምሯል።

እንደ ዘለቀ (ዶ/ር) ገለጻ፤ አሁን ላይ በኢስተርን ኢንዱስትሪ ፓርክ መዋለ ንዋያቸውን ፈሰስ በማድረግ ላይ ከሚገኙ 153 የውጭ ባለሀብቶች መካከል 95 ከመቶ የቻይና ቀሪዎቹ ደግሞ የሕንድና የእንግሊዝ ባለሀብቶች ናቸው።

በኢትዮጵያ አጠቃላይ ከ3 ሺህ 300 በላይ የሚሆኑ የቻይና ኩባንያዎች ከ8 ነጥብ 5 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ መዋለ ንዋይ ፈሰስ በማድረግ በሀገር ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ላይ አይነተኛ ሚና እየተጫወቱ እንደሚገኙ ያስረዳሉ።

የቻይና ኩባንያዎቹ በተኪ ምርት፣ በክህሎትና የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲሁም በንግድ ትስስር እያበረከቱት ከሚገኘው አስተዋፅዖ ባሻገር ከ325 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ ዕድል መፍጠር መቻላቸውን ይጠቁማሉ።

የሀገር ውስጥና የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት ኮሚሽኑ የድጋፍና ክትትል ሥራ እየሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ በዚህም በኢስተርን ኢንዱስትሪ ዞን የሚገኙ ባለሃብቶች በሚደረግላቸው የቅርብ ድጋፍ ለበርካታ ዜጎች የሥራ ዕድል በመፍጠር በኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ዕድገት የድርሻቸውን እየተወጡ ይገኛሉ ይላሉ።

የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያውም በኢትዮጵያ በኢንቨስትመንት ዘርፍ የተሰማሩ ባለሃብቶች የሚቀርቡ የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት ጥያቄዎችን ምላሽ በመስጠት ገንቢ ሚና እየተጫወተ እንደሚገኝ ነው ያስገነዘቡት።



# በክልሉ 14 ሚሊዮን ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

የሩዝ ልማት በበለጠ እንዲያድግ መሬቱ በዘመናዊ ትራክተር መታረስ እንዳለበት ጠቁመው ፤ የሩዝ መፈልፈያ ማሽን እጥረት ለሩዝ ልማት ተግዳሮት ከሆኑ ጉዳዮች አንዱ በመሆኑ ትኩረት ያስፈልገዋል ብለዋል።

አርሶ አደሩ ሩዝ አምርቶ ለማስፈልፈል አላስፈላጊ ወጪ እንደሚያወጣ ተናግረው፤ ችግሩን ለመፍታት የሚመለከታቸው  አካላት ትብብር እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል።

በባለፈው ዓመት የምርት ዘመን በክልሉ በሩዝ ሰብል የተሸፈነው ማሳ 82 ሺህ 270 ሄክታር መሆኑን ጠቁመው፤ ከዚህም  አራት ሚሊዮን 486 ሺ ኩንታል ሩዝ ምርት መገኘቱን አስታውሰዋል።

# “በአፍሪካ ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን ለመፍታት ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ለአፍሪካ ችግሮች አፍሪካዊ መፍትሔ የሚለው መርሕ መፈክር ከመሆን አልፎ በተግባር የሚገለጥ መሆኑንም አንስተዋል። በሰብዓዊ ርዳታና በሰብዓዊ መብት ተሚጋችነት ሽፋን የሚደረጉ የውጭ ጣልቃ ገብነት ችግሮችንም በጋራ መጋፈጥ እንደሚገባ ተናግረዋል። ለዚህ ደግሞ ቀጣናዊ ትብብር እና አብሮነት ላይ ትኩረት አድርጎ መሥራት ይገባል ብለዋል።

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መከላከያ ሚኒስትር ኢንጂነር አይሻ መሐመድ በበኩላቸው፤ በፀጥታው ዘርፍ ትብብርን በማጠናከርና ሽብርተኝነትን በመዋጋት የበለጠ አስተማማኝና ሠላም የሰፈነባት አፍሪካን መገንባት እንደሚገባ አስታውቀዋል።

ጉባኤው የአፍሪካ ሀገራት በትብብር በአሕጉራቸው በአስተማማኝ ፀጥታ ላይ ለመሥራት፣ ከሀገር አቀፍ ድንበሮች በላይ የሆኑ ጉዳዮች ላይ በቅርበት ለመሥራት እንዲሁም በመፃኢው የአፍሪካ ብልፅግና ላይ ያላቸውን ቁርጠኝነት ለማጉላት የሚረዳ መሆኑን ገልጸዋል።

በአፍሪካ ኅብረት የፖለቲካ ጉዳዮችና የፀረ-ሽብር ማዕከል ተወካይ ባባቱንዴ አባዮሚ በበኩላቸው፤ ሰው ሠራሽና የተፈጥሮ አደጋዎች፣ የፀጥታ ችግሮች፣ የፖለቲካ አለመረጋጋት፣ የጂኦ ፖለቲካ ፉክክርና ሌሎች ከፀጥታ ጋር የተገናኙ ችግሮች አሕጉሪቱን እየፈተኑ ይገኛሉ ሲሉ ተናግረዋል።

ለአፍሪካ የፀጥታ ችግሮች የአፍሪካ አባል ሀገራት በተጠናከረ የጋራ ትብብር ሊሠሩ እንደሚገባ አመላክተው፤ ጉባኤውም ለዚህ ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር ጠቁመዋል። የአፍሪካ ኅብረትም ለመሰል የትብብር ሥራዎች ድጋፉን አጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።




በጉባኤው ላይ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ተመስገን ጥሩነህ፣ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ፣ የተለያዩ ሚኒስትሮችና አምባሳደሮች እንዲሁም ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ተገኝተዋል።

በነገው ዕለት በሚጠናቀቀው ጉባኤ በአሕጉሪቱ ለሚከሰቱ ሰው ሠራሽና የተፈጥሮ አደጋዎች አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የጋራ አቅጣጫዎች፣ በቴክኖሎጂ ሽግግር ያሉ ዕድሎች ላይ የልምድ ልውውጥና ሌሎች አጀንዳዎች ላይ ጥልቅ ውይይት እንደሚደረግ ተገልጿል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የቡናው ዘርፍ ስኬት ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያው ውጤታማ መሆኑን አመላካች ነው !

ቡና በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ ያለውና 20 ሚሊዮን የሚጠጋ ሕዝብ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚተዳደርበት ዘርፍ ነው። በውጭ ምንዛሪ ረገድም ከሀገሪቱ የውጪ ምንዛሪ ከ35-40 በመቶ ይሸፍናል። ዘርፉ ተገቢውን ትኩረት ካገኘ ከዚህም በላይ በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ውስጥ የጎላ ድርሻ እንደሚኖረው ይታመናል።

ዘርፉ የሀገሪቱ የኢኮኖሚ ዋልታ ሲባል የቆየ ቢሆንም ባለፉት አምስት ዓመታት ያሳየው ለውጥ ግን የሀገር ዋልታነቱን በአግባቡ ያረጋገጠ ይመስላል። በተለይም ሀገር በቀል የኢኮኖሚ መርሐ ግብር እንደሀገር ከተተገበረበት ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ ቡና በሀገር ኢኮኖሚ ውስጥ የሚጫወተው ሚና እያደገ መጥቷል።

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ በ2012 ዓ/ም 270ሺ 035.1 ቶን ለውጪ ገበያ ቀርቦ 854.12 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ተገኝቷል። በ2013 ዓ/ም 243ሺህ 311 ቶን ለውጪ ገበያ ቀርቦ 907 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ተገኝቷል፤ በ2014 300ሺ ቶን ለውጪ ገበያ ቀርቦ 1.4 ቢሊዮን ዶላር ተገኝቷል፤ በ2015 240 ሺ 369 ቶን ለውጪ ገበያ ቀርቦ 1.3 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ሲገኝ ፤ በ2016 ዓ/ም 300 ሺ ቶን ለውጪ ገበያ ቀርቦ 1.43 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ተገኝቷል።

እንደ ሀገር የሀገር በቀል ኢኮኖሚው መተግበር ከመጀመሩ በፊት የቡና ግብይቱ በበርካታ ማነቆዎች የተተበተበ ነበር። በዋናነት የግብይት ሥርዓቱ በጣም የተንዛዛ፤ እሴት የማይጨምር እና ብዙ ችግሮች የነበሩበት ነበር። የሀገር በቀል ኢኮኖሚው ተግባራዊ መሆንም የግብይት ሥርዓቱን በማሳጠር በቡና ልማቱ እና ግብይቱ ላይ ለውጥ ሊመጣ ችሏል። ከዚህ ጎን ለጎንም በዓለም አቀፍ ገበያ ላይ ኢትዮጵያ ቡና የሚሸጥበት ዝቅተኛ የዋጋ ጎዳግ እንዲወሰንና አይነቱ ደረጃ እንዲኖረው መደረጉ የተሻለ የውጭ ምንዛሪ እንዲገኝ በር ከፍቷል።

ባለፉት 6 ዓመታት ከአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር ጋር በተያያዘ 8 ነጥብ 5 ቢሊዮን የቡና ችግኞች የተተከሉ ሲሆን ይህም የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር የአካባቢ መራቆትን ከመከላከል ጎን ለጎን ቡናን የመሳሰሉ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸው ምርቶች እንዲስፋፉም የራሱን አስተዋፅዖ አበርክቷል።

የቡና ችግኞችን በስፋት ከመትከል ጎን ለጎንም የቡናን ምርታማነት ሊያሳድጉ የሚችሉ የግብርና ስልቶች ተግባራዊ በመሆናቸውም ባለፈው ዓመት ብቻ 1 ሚሊዮን ቶን ቡና ለማምረት ተችሏል። ለውጭ ገበያ የሚቀርበው የባለ ልዩ ጣዕም ቡና ድርሻ ከነበረበት 30 በመቶ ወደ 60 በመቶ አድጓል።

የአፍሪካ ቀዳሚ የዓለም ደግሞ ሦስተኛ የአረቢካ ቡና አምራች የሆነችው ሀገራችን ባለፈው የበጀት ዓመት በቡና የውጪ ንግድ 1 ነጥብ 43 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር አግኝታለች። ይህም ሀገሪቱ በታሪክ አይታ የማታውቀው የገቢ መጠን ነው። ካለፈው ዓመት ልምድ በመነሳትም በ2017 በጀት ዓመትም ቡና አምና ካስገኘው የ1 ነጥብ 43 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር በመሻገር 2 ቢሊዮን ዶላር ለማስገባት ከወዲሁ ዕቅድ ተይዞ እየተሠራ ነው።

የቡናን ምርታማነትና የገበያ ድርሻ ከማስፋት ጎን ለጎንም የቡና አምራቾች ከዘርፉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የተሠራው ሥራ ውጤት እያሳየ በመምጣቱም በአሁኑ ወቅት ከ1 ሺህ በላይ የቡና አምራች አርሶ አደሮች ምርታቸውን በቀጥታ ለውጭ ገበያ በማቅረብ ጠቀም ያለ ገቢ እያገኙ ነው።

በአምራች አርሶ አደሮች አንድ ኪሎ ግራም ባለ ልዩ ጣዕም ቡና ከ100 ሺህ ብር በላይ እየተሸጠ ሲሆን ከቡና የእሴት ሠንሠለት የሚያገኙት ድርሻም እያደገ መጥቷል። ከአንድ ሺህ በላይ አርሶ አደሮች የላኪነት ፈቃድ በማውጣት የቡና ምርታቸውን በቀጥታ ለውጭ ገበያ እያቀረቡ ይገኛሉ።

ኢትዮጵያ የቡና አምራቾችን ተጠቃሚ ለማድረግ የሠራችው ሥራ ውጤት በማምጣቱ እና በዓለም ላይ የገበያ ድርሻዋም እየሰፋ ስለመጣ የጂ-25 ቡና አምራች ሀገራትን በሊቀመንበርነት የመምራት ዕድል ተጎናጽፋለች። በመምራት ላይም ትገኛለች። የአፍሪካ 2063 ስትራቴጂክ የንግድ ምርት ሆኖ እንዲሰየም ለኅብረቱ ጉባዔ ያቀረበችው ጥያቄም ተቀባይነት አግኝቷል።

የአፍሪካ ኅብረት ቡናን ዋነኛ ስትራቴጂክ ሸቀጥ አድርጎ መውሰዱ ከ70 በመቶ በላይ የሚሆነውን በቡና ላይ ኢኮኖሚውን የመሠረተውን የአፍሪካ ነዋሪ ከመጥቀሙም ባሻገር ኢትዮጵያን የመሳሰሉ ቡና አብቃይ ሀገራት የተፈጥሮ ሃብታቸውን በአግባቡ እንዲጠቀሙ የሚያነሳሳ ነው።

ኢትዮጵያ አሁን ላይ በቡናው ዘርፍ ያሳየችው እምርታ በእጅጉ የሚያበረታታ፤ እንደ ሀገር ተግባራዊ ያደረገችው ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ በየዘርፉ ትርጉም ያለው ውጤት እያመጣ መሆኑን በተጨባጭ ማሳያ ነው። ይህም ሆኖ ግን ሀገሪቱ የቡና መገኛ ከመሆኗ እና ተወዳጅ የሆኑ የቡና ዝርያዎች መገኛ ከመሆኗ አንጻር ለዘርፉ ከዚህ በላይ ትኩረት ከተሰጠው በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ውስጥ የሚኖረው ድርሻ ከዚህም የበለጠ እንደሚሆን ይታመናል!


## አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4200

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**

ወርቁ ማሩ

Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## የፍጻሜው ጅማሬ እውን እየሆነ ነው

**ወጋሶ**

ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ ተደጋግሞ ከብዙዎቻችን አንደበት የሚደመጥ አንድ ዓረፍተ ነገር አለ፤ ይኸውም “ሠላም ጠፋ!” የሚል ነው። በእርግጥም በሀገራችን ካሉ ጥቂት ከማይባሉ አካባቢዎች ውስጥ ከአንዱ ቦታ ወደሌላው ቦታ ለማቅናት በመጀመሪያ ወደአዕምሯችን የሚመጣው ስለአካባቢው ሁለት ሦስቴ ማሰብና ቀጥሎም “እዛ አካባቢ ምን አለ? ማን አለ?” የሚል ጥያቄ እንደሆነ እገምታለሁ።

“ምን” እና “ማን” የተባሉት አካላት ደግሞ በየአካባቢው መሣሪያ አንግተው የአካባቢውን ነዋሪ፣ ዘመድ ጥየቃም ሆነ ለግል ጉዳዩ ወደ አካባቢው የሚመጣውን፤ ከዛም አልፎ አካባቢውን አቋርጦ የሚያልፈውን ተጓዡ ሳይቀር አበሳ እያሳዩት ነው። የአካባቢው ነዋሪ በሠላም ወጥቶ በሠላም መግባት ብርቅ እንዲሆንበት እያደረጉ ነው።

በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ አንድ ላይ እንደሚያመለክተው፤ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወይም በሕጋዊ መንገድ ሀገሪቱ ውስጥ የሚገኝ የውጭ ዜጋ በመረጠው የሀገሪቱ አካባቢ የመዘዋወርና የመኖሪያ ቦታ የመመሥረት፣ እንዲሁም በፈለገው ጊዜ ከሀገር የመውጣት ነፃነት እንዳለው ይደነግጋል።

እነዚህ አካላት ለሕግ እና ሥርዓት ተገዥ የሆነ ማንነት የላቸውም። ዋነኛ ባሕሪያቸው ሽፍትነት ነው፤ ለዚህ ተራ ባሕሪያቸው ብዙዎችን አሰቃይተዋል፤ ገድለዋል፤ ዘርፈዋል፤ አሰጨንቀዋል። እትብታቸው ከተቀበረበት አካባቢ ጥለው እንዲኮበልሉ ምክንያት ሆነዋል።

እነዚህ ገድሎ/ዘርፎ አደር የሆኑ ኃይላት፤ የገዛ ሕዝባቸውን የእለት ተእለት ሕይወት ከማክበድ ባለፈ፤ በብዙ ዋጋ የተገነቡ መሠረተ ልማቶችን አፍርሰዋል፤ እያፈረሱም ነው። በተጨማሪ ልማቶች እንዳይከናወኑ ፈተና እየሆኑ ነው። በዚህም ተግባራቸው ደግሞ ደስተኞች መሆናቸው በየወቅቱ ከሚያሰሟቸው ፉከራዎች እና ቀረርቶዎች መረዳት ይቻላል።

በርግጥ ለነዚህ ኃይሎች በአንድም ይሁን በሌላ፤ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ አቅም የሆናቸው በእነሱ እኩይ ተግባር ሕይወቱ የተንሳቆለው ሕዝብ ስለመሆን ለመገመት የሚከብድ አይደለም። በተራ ፕሮፖጋንዳው ብዙዎችን የዓላማቸው መጠቀሚያ ማድረግ ችለዋል። በዚህም እድሜውን ማራዘም ችሏል።

አሁን ግን ሁኔታው መልኩን እየቀየረ ነው፤ ሕዝቡ የቡድኖቹን እውነተኛ ማንነት መረዳት ከጀመረ ውሎ አድሯል። በዚህም ሠላምን ለማስከበር የሚደረጉ ጥረቶች የተሻለ ውጤት እያስገኙ ነው። በዚህም እየተገኘ ያለው አዎንታዊ ሠላም ሕዝቡ ከትናንት ዛሬ የተሻለ የሠላም አየር እንዲተነፍስ እያስቻለው ነው።

ይህንን አንጻራዊ ሠላም አስተማማኝ እና ዘላቂ ለማድረግ፤ ሕዝቡ የነዚህን ኃይሎች ማንነት በአግባቡ በመረዳት፤ አንድነቱን አጠናክሮ ለሠላሙ ዘብ መቆም ይጠበቅበታል። ሕዝቡ ለሠላሙ እርስ በእርስ መደጋገፍ ከቻለ የትኛውም አካል ሠላሙን ሊያውክ፤ አደጋ ውስጥ ሊከተው አይችልም ።

ሕዝቡ ስለሠላሙ መጠበቅ ያለበት ከቀበሌው ሲቀመንበር ወይም ደግሞ ከወረዳው ሠላምና ደኅንነት ጽሕፈት ቤት፤ እልፍ ሲልም ከክልሉ የሠላምና የፀጥታ ቢሮ መሆን የለበትም። እያንዳንዱ ለአካባቢው ሠላም መስፈን የራሱን አስተዋፅዖ ማበርከት ይጠበቅበታል። በዙሪያው ያሉ ሠላም ነሺዎችን አምርሮ በቃችሁ ሲላቸው ይገባል

ሕዝቡ ስለሠላሙ መጠበቅ ያለበት ከቀበሌው ሊቀመንበር ወይም ደግሞ ከወረዳው ሠላምና ደኅንነት ጽሕፈት ቤት፤ እልፍ ሲልም ከክልሉ የሠላምና የፀጥታ ቢሮ መሆን የለበትም። እያንዳንዱ ለአካባቢው ሠላም መስፈን የራሱን አስተዋፅዖ ማበርከት ይጠበቅበታል። በዙሪያው ያሉ ሠላም ነሺዎችን አምርሮ በቃችሁ ሊላቸው ይገባል።

ገና ከጅምሩ፣ ከአንድ ገጠር ቀበሌ ተነስቶ ወደ አንድ ወረዳ የሚሔድን የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ተሽከርካሪ እዛው እበራችን ላይ ማስፈራራትና ማገት ሲጀምሩ ዝም! ያልነው ራሳችን ነን፤ መሠረተ ልማቱን ሲያበላሹና ዘርተን እንዳናጭድ እንቅፋት ሆነው ሲደነፉ ጭጭ! ያልነው እኛው ነን።

ይህ ነገር ውሎ አድሮ የራሳችንን ልጆች እንደሚሰለቅጥ መገመት የተሳነን ከእኛ ሌላ ማን ሊሆን ይችላል? አሁን አሁን እንደልብ ወጥተን ማረስ፣ መዝራት፣ መኅልኅል፣ ማጨድና መሰብሰብ የተሳነን ሁኔታ ተፈጥራል። ልጆቻችንም ቢሆኑ ወደትምህርት ቤት ሔደው እንዳይማሩ ዕድሉ እየጠበበ መጥቷል።

ከዚህ በኋላ ለሠላማችን የምናባክናት አንዲትም ደቂቃ ልትኖር አይገባም። እስከዛሬ ድረስ በብዙ ቆስለናል፤ ይህ የደረሰብን ቁስል ወደማመርቀዙ ሔዶ መድኃኒቱ ከመታጣቱ በፊት ከሠላማችን ጋር ልንስማማ ይገባል። ለሠላም ዘብ የቆሙ ወንድሞቻችንንና ልጆቻችንን ማገዝ ይጠበቅብናል።

ሠላም ከምንም ነገር በላይ ነው። አምርተን እንዳንበላ እንቅፋት፤ ወጥተን እንዳንገባ ጋሬጣ የሆኑብንን የሠላም ጠንቆች ከመካከላችን እናስወግድ። ወደንም ሆነ ተገድደን በጉያችን ታቅፈናቸው የነበሩት የሠላም ቀበኞች ጉያችን እንዲሞቃቸው አናድርግ።

ከሰሞኑን አዲሱ የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት አምባሳደር ታዬ አፅቀ ሥላሴ፣ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የፌዴሬሽን ምክር ቤት 4ኛ ዓመት የሥራ ዘመን የመክፈቻ ሥነ ሥርዓት ላይ ተገኝተው ባደረጉት ንግግር፤ “ዘላቂ ሀገራዊ ሠላምን ማስፈንና የሕግ የበላይነትን ማረጋገጥ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች ናቸው” ብለዋል። ለሚገነባው ዘላቂ ሠላም ሁሉም የድርሻውን መወጣት እንዳለበትም አመልክተዋል።

የትኛውም ጥያቄ ያለው አካል ጥያቄውን በሕግ አግባብ ማቅረብ ይችላል፤ ይሕ ሕገመንግሥታዊ መብት ነው። ፍላጎቶቹን በጠብመንጃ አማካይነት በሕዝብ እና በመንግሥት ላይ ለመጫን የሚደረግ ጥረት ግን ሀገር እና ሕዝብን የሚጎዳ፤ በዚህ ዘመን ጥፋት እንጂ ለጥያቄ መልስ ሊያመጣ የሚችል አይደለም።

መንግሥት፤ ከየትኛውም ኃይል ጋር በየትኛውም ጊዜ እና ቦታ በችግሮች ዙሪያ ለመወያየት ፈቃደኛ መሆኑን ደጋግሞ አስታውቋል። “እንነጋገር፤ እንወያይ” ሲል የሠላም እጁን ዘርግቶ ሲጠብቅ ሰንብቷል። አሁንም ቢሆን በሩ አልተዘጋም። ለሕዝቡና ለሀገር ሠላም ሲል መንግሥት ልቡን አስፍቶ እየጠበቀ ነው።

አዲሱ የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንትም ያረጋገጡት ይህንኑ ነው። እንዲያውም በተናጠልም ይሁን በጋራ መንግሥት በሠላማዊ መንገድ ለመነጋገር ሁልጊዜ ዝግጁ መሆኑንም በመክፈቻ ንግግራቸው ጠቅሰዋል።

ኅብረተሰቡም ከመነሻው የሚፈጠር የሠላም መደፍረስ ማን እንደፈጠረው ጠንቅቆ ስለሚያውቅ ሠላም አደፍራሹን አካል “ሃይ” ሊለው ይገባል። ምንጩ ላይ በመሆን ከፀጥታ ኃይሎች ጋር በመተባበር ከተሠራ ችግሩን በእንጭጩ መግታት ይቻላል። ይህ ደግሞ ከግጭት ለማትረፍ የሚንቀሳቀሱ ኃይሎችን አቅም የሚያሳጣ ነው ።

ግራም ነፈሰ ቀኝ ኢትዮጵያ ጥቂቶቹ ከፈጠሩት ውጥንቅጥ መውጣቷ አይቀሬ ነው። በተለያየ አቅጣጫ ጦር የሚያነሱና የሕዝቡን የመልማት ተስፋ የሚናጠቁ ኃይሎች ጊዜያቸው ያበቃል። የገዛ ወገኖቻቸውን እያስጨነቁና እያሰቃዩ አይቀጥሉም። ለዚህም የፍጻሜው ጅማሬ እውን እየሆነ ነው።

# ‹‹በዩኒቨርሲቲው አመራር ድክመት የመመረቂያ ጊዜያችን እንዲራዘም ተደርጓል››

- በወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ተማሪዎች

# ‹‹በዩኒቨርሲቲው የተደረገ የኘሮግራም መዛባት የለም››

- የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ

**በመልካም አስተዳደርና ምርመራ ቡድን**

የዛሬው የፍረዱኝ አምድ ዝግጅታችን ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ይወስደናል። በወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ አመራሮች እና በጤና ሳይንስ ተማሪዎች መካከል የተፈጠረን ውዝግብ ያስመለክተናል።

‹‹በወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ አመራሮች ድክመት እና በፕሮግራም ያለመመራት ችግር መመረቅ በነበረብን ጊዜ መመረቅ አልቻልንም። ዩኒቨርሲቲው አመራሮች በደል እየፈጸሙብን ነው›› ሲሉ የጤና ሳይንስ ተማሪዎች ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አዲስ ዘመን ጋዜጣ የመልካም አስተዳደር እና ምርመራ ቡድን አቤት ብለዋል።

የምርመራ ቡድኑም የተማሪዎቹን ቅሬታ እና የዩኒቨርሲቲው አመራሮች ምላሽን ይዟ ቀርቧል።

**ከአቤቱታ አቅራቢዎች አንደበት**

ለምርመራ ቡድኑ አቤቱታ ያቀረቡት ተማሪዎች በርካታ ቢሆኑም ተፈጸመ የተባለውን ችግር ያሳያሉ ያልናቸውን የተወሰኑ ተማሪዎች አቤቱታ ወስደናል። ተማሪዎቹ ስማቸውም እንዳይጠቀስ ስለጠየቁ ስማቸው አልተገለጸም።

**አቤቱታ አቅራቢ - አንድ**

አቤቱታ አቅራቢ አንድ እንደገለጸው፤ ወደ ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ የገባው በ2015ዓ.ም። በዩኒቨርስቲውም በጤና ፋካሊቲ በፋርማሲ ትምህርት ክፍል ተመደበ። ይሁን እንጂ እሱ እና ጓደኞቹ ትምህርት በጀመሩበት ዓመት የአንድ መንፈቀ ዓመት ትምህርት ብቻ ተምረው ወደ ቤተሰብ እንዲሄዱ ተደረገ። በሌሎች ዩኒቨርሲቲ ተመድበው የነበሩ ጓደኞቻቸው ግን የሶስት መንፈቀ ዓመት ትምህርት መማር ችለው ነበር። ቀጥሎ በነበረው የትምህርት ዘመንም እንዲሁ በአንድ ዓመት መማር የነበረባቸውን ያህል ሳይማሩ ቀሩ።

በዚህም አሁን ላይ ከአቤቱታ አቅራቢው ጋር የ12ኛ ክፍል ፈተና ተፈትነው ወደ ሌላ ዩኒቨርሲቲ ከገቡ ጓደኞቻቸው አንድ ዓመት ወደኋላ መቅረታቸውን እና ይህም ከቤተሰብ ጀምሮ እስከ ሰፈር ሰዎች በሚመጣ አስተያየት ለከፍተኛ የሥነ ልቦናዊ ጉዳት እና ተጽእኖ መዳረጋቸውን ይናገራል። አሁን ላይ እየሄዱበት ያለውም የትምህርት አሰጣጥ ሌላ አንድ ዓመትን ወደኋላ እንደሚጎትታቸው ያስረዳል።

በ2015 ዓ.ም ላይ ዩኒቨርሲቲው ያወጣው የትምህርት መርሃ ግብር "ስኬጁል" በራሱ ልክ አልነበረም። ለመዘግየታቸው ዋና ምክንያት እሱ ነው። በወቅቱ የወጣው የትምህርት መርሃ ግብር ‹‹ትክክል አይደለም›› ብለው ተማሪዎች ቅሬታ ቢያቀርቡም ሰሚ አለማግኘታቸውን ያስረዳል። አንድ የፋርማሲ ተማሪ አምስት ዓመት መማር ሲገባው ስድስት ዓመት እና ከዚያ በላይ እንዲማር እየተደረገ ነው።

አሁንም የትምህርት አሰጣጡ በመጓተቱ የተነሳ አንድ ተማሪ መመረቅ ካለበት አንድ ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆነ ጊዜ ዘግይቶ ይመረቃል። እሱንም ከዚህ በኋላ በተገቢው መንገድ የትምህርት መርሃ ግብር አውጥተው ማስተማር ከቻሉ ነው።

ዩኒቨርሲቲው በስኬጁል እንደማይመራ አንዱ ማሳያ ደግሞ ተማሪዎችን ከእረፍት ለትምህርት ጥሪ የሚያደርጉበት ማስታወቂያ ነው። ለምዝገባ ቁርጥ ያለ ቀን ወስነው ተማሪዎችን አይጠሩም። ወደ ዩኒቨርሲቲው ለመድረስ ከ7 መቶ ኪሎ ሜትር እንደሚጓዝ የሚናገረው አቤቱታ አቅራቢ ተማሪ ፤ ዩኒቨርሲቲው ባወጣው ማስታወቂያ መሰረት ወደ ዩኒቨርሲቲ ግቡ በተባለበት ጊዜ እየመጣ መንገድ ላይ እያለ ዩኒቨርሲቲው ምክንያቱ በውል ባልታወቀ አግባብ የመግቢያ ጊዜውን አራዘመ። በዚህም ምክንያት በርካታ ቀናት አዲስ አበባ ላይ አልጋ ተከራይቶ እንዲቆይ ተገደደ። ይህም ላልተገባ ወጪ መዳረጉን ያስረዳል። በየጊዜው የመግቢያ ቀን እያሳወቁ መቀያየር ለወላይታ ዩኒቨርሲቲ አዲስ አይደለም።

**ቅሬታ አቅራቢ - ሁለት**

ሁለተኛው ቅሬታ አቅራቢው የፋርማሲ ተማሪ ሲሆን ተማሪዎች የሚለማመዱባቸው የላብራቶሪ እቃዎች ብዙ ጊዜ እንደማይሟሉ ይነገራል። በላብራቶሪው ኬሚካሎችም የሉም። ጋዋንም ተበዳድረን ነው የምንለብሰው <<ለምን እንደዚህ ይደረጋል?>> ብለው ሲጠይቁ በየጊዜው ከበጀት ጋር የተያያዘ ችግር እንዳጋጠማቸው ይነገሯቸዋል።

ባለፈው ዓመት ከዚህ ቀደም የነበረው ማኔጅመንት (አመራር) ተቀይሯል። አዲስ ማኔጅመንት (አመራር) ሲመጣ ለውጦች ይኖራሉ ብለው ተስፋ አድርገው እንደነበረ ፤ ነገር ግን ምንም ለውጥ እንደሌለ አሁንም ሁሉም ነገር በነበረት እየቀጠለ መሆኑን ያስረዳሉ።

የህክምና ትምህርት ‹‹ኮርስ›› ብዛት ስላለው ትምህርቱን በተባለው ጊዜ ለመጨረስ ተማሪዎች ክረምቱን ጭምር ዩኒቨርሲቲ መቆየት ነበረባቸው። በኢትዮጵያ የሚገኙ ሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች ላይ ያለው ተሞክሮ ይህ ነው። የወላይታ ዩኒቨርሲቲ ግን ተማሪዎችን ግቢ ውስጥ እንዲቆዩ ቢያደርግም ለትምህርቱ መሟላት የነበረባቸው ግብዓቶች ባለመሟላታቸው መማር የነበረባቸው ትምህርት ማግኘት እንዳልቻሉ ያስረዳሉ።

መምህራኖቻቸው እና ‹‹ዲፓርትመንት ሄዶች ››(የትምህርት ክፍል ኃላፊዎች) በሚችሉት ልክ በስኬጁሉ ለማስተማር ይሞክራሉ። ነገር ግን በመማር ማስተማሩ ሂደት እያገጠሙ ያሉ ችግሮችን ከላይ ያለው አመራር የሚገነዘብ አይመስልም።

በወላይታ ዩኒቨርሲቲ ‹‹ኦቶና›› ተብሎ በሚጠራው ካምፓስ ተማሪዎች መመረቅ ካለባቸው ጊዜ አንድ ዓመት ተኩል እና ከዚያ በላይ ዘግይተዋል። የሰላም እጦት ችግር ባለባቸው አካባቢዎች እንኳን ተማሪዎች በጊዜ እንዲገቡና እንዲማሩ ይደረጋል። ወላይታ ላይ ግን ምንም ዓይነት የጸጥታም ሆነ የደህንነት ስጋት ሳይኖር ወጥ የሆነ ስኬጁል በማውጣት ተማሪዎችን እያስተማሩ አለመሆናቸውንም ያስረዳሉ።

የዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ደስ እንዳለው የትምህርት መርሃ ግብር ያወጣል። አንዳንድ ጊዜ በጣም ያፋጥኑትና ማወቅ ያለባቸውን ሳያውቁ እንዲሄዱ ይደረጋል። በሌላ ጊዜ ደግሞ በጣም ያጓቱትና ወደ ኋላ እንደሚቀሩ ይገልጻሉ።

አስተዳደሩ ለተማሪዎች የመመረቂያ ጊዜ መዘግየት ምንም ትኩረት አይሰጥም፤ በመዘግየት ውስጥ ሊፈጠሩ የሚችሉ ችግሮችን የሚያስቡት ሁሉ አይመስሉም። ሁሉን ነገር እንደ ቀልድ ነው የሚያዩት። የተማሪዎች እዚያ መቆየት እና ዘግይቶ መመረቅ ማግኘት ያለባቸውን እውቀት እንዲያገኙ ቢያስችል መልካም ነበር። ነገር ግን ዝም ብለው ጊዜ እያቃጠሉ መሆናቸውን ይናገራሉ።

እንደ የትምህርት ክፍሉ የሚለያይ ቢሆንም ዋናው ግቢም የሚማሩ ተማሪዎች መመረቅ ከነበረባቸው ጊዜ በአንድ ሴሚስተር ብቻ ነው የሚዘገዩት። በዚህም ዋናው ግቢ ላይ ያሉ ተማሪዎች ከዚህ በፊት ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ ሞክረው ነበር ፤ ግን የሚሰማ አካል ሊገኝ አልቻለም።

**ቅሬታ አቅራቢ - ሶስት**

በ2012 ዓ.ም ወደ ዩኒቨርሲቲው የገቡ የጤና ተማሪዎች በ2016 ዓ.ም ሰኔ ወር ላይ መመረቅ ሲገባቸው አሁንም በግቢው ይገኛሉ። ይህ የሆነው በዩኒቨርሲቲው ችግር ነው። በ2013 ግቢ ከገቡ ተማሪዎች መካከል መሆኑን የሚናገረው ቅሬታ አቅራቢዋ፤ ሌላ ዩኒቨርሲቲ የገቡ ተማሪዎች 2016 ዓ.ም መጨረሻ ላይ ተመርቀው ወጥተዋል። እነሱ ግን መቼ እንደሚመረቁ እንኳን እንደማያውቁ ትናገራለች።

በሁሉም ዩኒቨርሲቲ የሚገኙ የጤና ተማሪዎች በክረምት እየተማሩ እያለ የወላይታ ዩኒቨርሲቲ ግን ወደ ቤተሰብ ለመሄድ የሚሆን የአንድ ቀን ማስጠንቀቂያ እንኳን ሳይነገራቸው በአንድ ቀን ከግቢ እንዲወጡ ተደርጓል። ዩኒቨርሲቲው ሰኔ 18/2016 ዓ.ም ባወጣው ማስታወቂያ ‹‹ ሰኔ 19 ጠዋት በአስቸኳይ ግቢውን ለቃችሁ ውጡ›› የሚል ነበር።

በዚህም ምክንያት ምንም ዝግጅት ያላደረጉት ተማሪዎች ሰኔ 19 ጠዋት ተገደው ከዩኒቨርሲቲው ግቢ እንዲወጡ ተደረገ። በወቅቱ ‹‹እንዴት በአንድ ቀን ውጡ እንባላለን?›› የሚል ጥያቄ አንስተው እንደነበር የሚናገረው አቤቱታ አቅራቢዋ ፤ ‹‹ሁለት ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ መልሰን እንጠራችኋለን›› የሚል ምላሽ እንደተሰጣቸው ትናገራለች።

ይህን ተከትሎ በተለይም ከዩኒቨርሲቲው በበርካታ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ቤተሰቦቻቸው የሚገኙ ተማሪዎች ለሁለት ሳምንት ወደ ቤተሰቦቻቸው ከሚሄዱ እዚያው በዩኒቨርሲቲው አካባቢ ለመቆየት በመወሰን ቤት ተከራይተው መጠበቅን መረጡ። ነገር ግን የተባለው ጊዜ ሲደርስ ቢጠይቁም ‹‹ሌላ ሁለት ሳምንት ጠብቁ›› የሚል ምላሽ እንደተሰጣቸው ታስረዳለች።

ይሁን እንጂ አሁንም ከሁለት ሳምንት በኋላ ቢጠይቁም ለጉዳዩ ምላሽ የሚሰጥ አካል አለማግኘታቸውን ትናገራለች። በዚህም ከሶስት ወር በላይ ያለ ትምህርት እንዲቀመጡ መደረጋቸውን ትገልጻለች። ለጤና ተማሪ ይሄን ሁሉ ወር ያለ ትምህርት እንዲያልፍ የሚያደርግ ዩኒቨርሲቲ አለመኖሩንም ታስረዳለች።

አሁን ላይ በሌላ ዩኒቨርሲቲ ከሚማሩ አቻ ጓደኞቻችን ከአንድ ዓመትና ከዚያ በላይ ለሚሆን ጊዜ ወደኋላ መቅረታቸውን ነገር ግን አሁንም ከዚህ የከፋ ችግር እንዳያጋጥማቸው ስጋት ውስጥ መሆናቸውን ጠቁማለች። ዩኒቨርሲቲው በበርካታ ውስብስብ ችግሮች የተሞላ ነው የምትለው አቤቱታ አቅራቢዋ ፤ ግቢ ውስጥ ያለው የሴቶች ማደሪያ ህንጻ አንድ ብቻ መሆኑን እና በሚኖሩበት ህንጻ ‹‹ዶርም›› ውስጥ ደግሞ ሎከር እንኳን አለመኖሩን ትገልጻለች።

በአንድ ክፍል ውስጥ ስድስት እና ሰባት ተማሪ ሆነው እንደሚኖሩ የምትገልጸው ተማሪዋ፤ ውድ የሆኑ እንደ ላፕ ቶፕ፣ ታብሌት እና የትምህርት ቁሳቁሶችን የሚያስቀምጡበት ቦታ እንደሌላቸው ታስረዳለች። በአጠቃላይ ዩኒቨርሲቲው ተማሪዎችን ለማስተማር የተዘጋጀ እንደማይመስል አመላክታለች።

በግቢ ውስጥ ተማሪዎች የሚዝናኑባቸው ካፌዎች ሁለት ብቻ ናቸው። አንዱ በዩኒቨርሲቲው የሚታከሙ የውጭ ህሙማን ጭምር የሚጠቀሙበት ነው። ሌላኛው ደግሞ ጥሩ ምግብ የለውም ፤ በዚያ ላይ ገበያ ስለሚበዛ ወረፋ አለው። ለጤና ተማሪ ቆሞ የሚጠብቅበት ጊዜ አይኖረውም።

ይህን ሊረዳ የሚችለው የጤና ተማሪ ብቻ ነው። ‹‹ግቢው ሰፊ ሆኖ እያለ ተጨማሪ ምግብ ቤቶችን ከፍተው ተማሪዎች ሳይንገላቱ አገልግሎት የሚያገኙበትን ሁኔታ እንዴት ማመቻቸት ይከብዳቸዋል?>> ስትል ትጠይቃለች።

**ቅሬታ አቅራቢ- አራት**

ዩኒቨርሲቲ ሲባል የቅንጦት ስፍራ እንዳልሆነ እናውቃለን የሚለው ሌላኛው ቅሬታ አቅራቢ፤ በግቢው ጂ+6 የሆነ የወንድ ተማሪዎች ማደሪያ መኖሩን ተናግሮ፤ ህንጻው መታጠቢያ ቤት የለውም ይላል። መታጠቢያ ቤቱ ላይ ያለው ውሃ ሲፈስ የህንጻው አሰራር ችግር ስላለበት ህንጻው በውሃ ይጥለቀለቃል።

ከዚህ የተነሳም ‹‹የኢንተርን›› ተማሪዎች ካሉበት ህንጻ በመሄድ እንደሚታጠቡ ያስረዳል። ይህም ሆኖ የተማሪዎችን ችግር መቅረፍ ያልቻለው አመራር በልዩ ሁኔታ ከሚማሩት ተማሪዎች ህንጻ ሄዳችሁ እንዳትታጠቡ የሚል ማስታወቂያ ተለጠፈ።

ይህን ተከትሎ ተማሪዎች በህብረት በመሆን የት ሄደን እንታጠብ? የሚል ጥያቄ ማንሳታቸውን እና በተማሪ ህብረት አማካኝነት ተከራክረው ፈቃድ ማግኘታቸውን ያስረዳሉ። ‹‹በአጠቃላይ አመራሮቹ የሚሰሩትን ሥራ የሚያውቁት አይመስለኝም›› ሲል ይናገራል።

በግቢው የውሃና የመብራት ችግር የለም የሚለው አቤቱታ አቅራቢው ፤ ነገር ግን ውሃው ቢኖርም ወንዶች ህንጻ ላይ ያለው ችግር መቅረፍ አለመቻላቸውን ይገልጻል።

ለተማሪዎች የሚቀርበው ምግብ በየጊዜው ጥራቱ እየቀነሰ ነው። ይሄ ሁሉ ችግር እያለ ግን የተማሪዎች ትኩረት ትምህርቱ በተቀመጠለት የጊዜ ሰሌዳ እንዲያልቅላቸው መሆኑን ያስረዳል። አራት ዓመት መማር ያለበት በአራት ዓመት ውስጥ ትምህርቱን መጨረስ አለበት ፤ አምስትም ዓመት መማር ያለበት በአምስት ዓመት ትምህርቱን ተምሮ ማጠናቀቅ እንዳለበት ይገልጻል።

በኮቪድ ወቅት ማለትም የ2012 ዓ.ም ወደ ዩኒቨርሲቲው የገቡ ተማሪዎች እስካሁን አልተመረቁም። በሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች ያሉ ተማሪዎች ግን መደረግ ያለበትን ሁሉ አድርገው ለአንድ የጤና ተማሪ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ አስመርቀዋል። ወላይታ ዩኒቨርሲቲ ግን ከተፈጥሮ ሳይንስ ተማሪዎች የኢንጂነሪንግ ተማሪዎችን ብቻ ነው ያስመረቀው።

ለምሳሌ በ2013ዓ.ም ላይ ወደ ዩኒቨርሲቲው የገባ አንድ የጤና ተማሪ አሁን ላይ ቢያንስ አራተኛ ዓመት ሁለተኛ ሴሚስተር ላይ መሆን ነበረበት። ነገር ግን ገና የሶስተኛ ዓመት ሁለተኛ ሴሚስተር ትምህርት እየወሰዱ መሆናቸውን ይናገራል። በዚህ ዓመት ይጨርሱ ቢባል እንኳን ማወቅ የሚገባቸውን ሳያውቁ የሚያልፉ መሆናቸውን አመላክቷል። 2014ዓ.ም ግቢ የገቡ ጤና ተማሪዎች ደግሞ ሶስተኛ ዓመትን መጨረስ ሲኖርባቸው አሁን ላይ ገና ሁለተኛ ዓመትን እየጨረሱ ነው።

‹‹አሁን ከዚህ የከፋ ችግር እንዳይገጥም ምን ማድረግ ይገባል?›› ብለው በክፍል ተወካዮቻችን አማካኝነት ከትምህርት ክፍሉ ኃላፊዎቻችን ጋር መወያየት ቢችሉም የትምህርት ክፍሉ ኃላፊዎችም ‹‹እኛ ምንም ማድረግ አንችልም›› የሚል ምላሽ እንደሰጧቸው ይናገራል።

ተማሪዎች ግቢ ውስጥ በቆዩ ቁጥር ተማሪው ላይ ከሚያደርሰው ጫና ባለፈ መንግሥትንም ላልተፈለገ ወጪ የሚዳርግ ነው። ይህ ደግሞ ለአዲስ ገቢ ተማሪዎች የሚበጀተውን በጀት የሚጎዳ ነው። ነገር ግን ይሄንን ታሳቢ አድርጎ በጣም ወሳኝ ለሚባሉ ትምህርቶች ሰፋ ያለ ጊዜ፤ ተጓዳኝ (ማይነር) የሚባሉትን ደግሞ አጠር ያለ ጊዜ ሰጥቶ የትምህርት ክፍለ ጊዜውን ለማስተካከል የሚጥር አንድም አመራር አለመኖሩን ጠቁሟል።

አንድ ተማሪ አንድ ዓመት እና ከዚያ በላይ ወደኋላ ቀርቷል ሲባል የዩኒቨርሲቲው አመራሮች አያውቁም ወይስ ለተማሪዎቻቸው አይጨነቁም ወይስ ችግሩ ከነሱ አቅም በላይ ሆኖ ነው? የሚለውን ማወቅ እንደሚፈልጉ የገለጸው፤ አቤቱታ አቅራቢው እንደዚህ ዓይነት ችግሮች ሲፈጠሩ ፕሬዚዳንቱ በዩኒቨርሲቲው እየሆነ ያለውን ታች ድረስ ወርዶ መመልከት እንደነበረበት ይናገራሉ።

**ቅሬታ አቅራቢ -አምስት**

በ2017 መጨረሻ ላይ መመረቅ የነበረበት። ነገር ግን አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ 2019 አጋማሽ ላይ እንኳን መመረቁን እርግጠኛ አይደለም። ችግሩ ከቤተሰብ እና ከራሳቸው እቅድ ውጭ እያደረጋቸው መሆኑን ያስረዳል። ይህም ለከፋ ‹‹ዲፕሬሽን›› ውስጥ እንዳስገባው ይናገራል። በተመሳሳይ የትምህርት ክፍል ከእርሱ ጋር ወደ ዩኒቨርሲቲ ገብተው የነበሩ ጓደኞቹ አሁን ላይ ተመርቀው ሥራ ይዘዋል። ይሄንን የተመለከቱ ቤተሰቦቹ አፍ አውጥተው ለምንድነው የማትመረቁት? ተባረህ ወይም ሌላ ችግር ገጥሞህ ከሆነ ንገረን ብለው እንደሚያስጨንቁት ጠቁሟል። በዚህም ተመርቀው ለቤተሰቦቻችን ተስፋ እንሆናለን ብለው ቢያስቡም ሃሳቡ ሃሳብ ብቻ ሆኖ መቅረቱን ይናገራል።

ኢትዮጵያዊ ቤተሰብ ልጆቹን እንዴት ሆኖ እንደሚያስተምር ይታወቃል። ተመርቀው እና ሥራ ተቀጥረው ቤተሰብን ማገዝ ባይችሉም እንኳን እራሳቸውን ችለው የቤተሰቦቻቸውን ጫና መቀነስ እንደነበረባቸው ጠቁመዋል። በየጊዜው ይሄ ነው በማይባል ምክንያት የትምህርት ጊዜው ስለሚራዘም መቼ እንደሚያልቅ እንደማያውቁ እና የምርቃት ጊዜያቸውን እንደሚናፍቁም

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# ፍረዱኙ

## ‹‹በዩኒቨርሲቲው አመራር ድክመት የመመረቂያ ጊዜያችን...

ከ6ኛ ገፅ የዞረ

ተናግሯል።

ግቢ ውስጥ በርካታ ተማሪዎች ተስፋ ቆርጠዋል። በኛ ግቢ (የጤና ተማሪዎች ካምፓስ) ትንሹ ተማሪ ግቢ ውስጥ የሚቆይበት አራት ዓመት ነው። ትልቁ ደግሞ ‹‹ሜድስን›› ሰባት ዓመት ነው። አሁን ግቢ ውስጥ ያሉ የሜድስን ተማሪዎች ከሰባት ዓመት በላይ ሆኗቸዋል፤ መቼ እንደሚመረቁ አያውቁም።

የትምህርት ክፍል ኃላፊዎች የተማሪዎችን ችግር የሚረዱ ቢሆንም ጉዳዩን ለበላይ በማሳወቅ መብቶቻቸውን ማስከበር ቢገባቸውም ለበላይ አመራሮች ከማሳወቅ ይልቅ ስለችግሩ ተማሪዎችን ማስረዳትን ነው የሚመርጡት። ለጤና ተማሪ በሳምንት ሁለት ፈተናና አንድ ‹‹ፕረዘንቴሽን›› ግድ ነው። በመሆኑም ችግር ቢገጥማቸው እንኳን ቅሬታ ለማቅረብ ጊዜ እንደሌላቸው ያስረዳሉ።

አሁን ላይ አዲስ ገቢ የጤና ተማሪዎች የሚገቡት ከጤና ካምፓስ ውጭ በዋናው ግቢ ነው። ዋናው ግቢ ደግሞ የኢንጂነሪንግ እና የማህበራዊ ሳይንስ ተማሪዎች መማሪያ ነው። በመሆኑም አዲስ ገቢ ተማሪዎች ‹‹ከሲኒየር›› የጤና ተማሪዎች ማግኘት የነበረባቸውን እውቀት እና ልምድ አያገኙም።

የመጀመሪያ ዓመት የትምህርት ውጤቱ ቀንሶብኝ ነበር የሚለው አቤቱታ አቅራቢው ፤ እንዴት ማጥናት እንደነበረብን፤ እንዴት እንደምንፈተን፣ እንዴት መዘጋጀት እንደነበረብን የምንጠይቀው ‹‹ሲኒየር›› አልነበረንም። አሁንም ይሄንኑ አሰራር እያስቀጠሉ ነው። ይህም የሆነው ነባር ተማሪዎች ትምህርት ሚኒስቴር ባስቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ተመርቀው ግቢውን ባለመልቀቃቸው ነው።

### ቅሬታ አቅራቢ -ስድስት

የሰፈሩ ልጅ የሆነው እና 12ኛ ክፍልም አብሮት የተማረው ጓደኛው ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ኮምፒዩተር ሳይንስ እየተማረ ነው፤ ዘንድሮ ይመረቃል። እየተማረው ባለው ትምህርት ሳይመረቅ ጥሩ ገንዘብ ያገኛል። ምክንያቱም ‹‹ዌብሳይት›› ይፈጥራል፤ ሌላም ከኮምፒዩተር ጋር የተገናኙ ሥራዎችን ይሰራል። ይህ ጓደኛው 12ኛ ክፍልን እንደጨረሱ የጤና ትምህርት ለመግባት ይፈልግ ነበር። ነገር ግን ውጤቱ ሳያስገባው ቀረ። ‹‹አሁን ላይ እኔ ሥራ ልሥራ ብል የሰው ሕይወት ላይ ስለሆነ የምንሰራው ምንም ነገር የለም። ወረቀቴን ሳልይዝ ሥራ የሚቀጥረኝ የለም። ››

በትምህርት ክፍላቸው ትምህርት ተጀምሯል ተብሎ መምህር ቢመደብም ብዙ ጊዜ መምህሩ ወደ ክፍል የሚገባው ትምህርት ተጀመረ ከተባለበት ጊዜ ከወር ከሁለት ወር በኋላ ነው። ‹‹ለምን?›› ብለው ሲጠይቁም፤ ‹‹መምህራን ደሞዝ አልተለቀቀም›› የሚል መልስ እንደሚሰጧቸውም ያስረዳል።

በግቢው ጠንካራ የተማሪ ህብረት የለም የሚለው አቤቱታ አቅራቢው፤ የተማሪዎች ህብረት የተማሪዎችን ችግር አይተው ለተማሪ ከመከራከር ይልቅ ለዩኒቨርሲቲው መወገንን እንደሚመርጡ አመላክቷል።

### የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ምላሽ

የዝግጅት ክፍሉ የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ የመማር ማስተማሩ ሂደት ምን እንደሚመስል፤ ተማሪዎች ያነሷቸውን ቅሬታዎች ታውቃላችሁ? ስንል ለዩኒቨርሲቲው የአካዳሚክስ ጉዳዮች ተጠባባቂ ምክትል ፕሬዚዳንት ዶ/ር አክበር ጭፎ ጥያቄ አቅርበን የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተውናል።

ዩኒቨርሲቲው የመማር ማስተማር ሥራው የሚያከናውነው የትምህርት ሚኒስቴር ባወጣው የጊዜ ሰሌዳ /ካሌንደር/ መሰረት አድርጎ ነው። ትምህርት ሚኒስቴር ለሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች በሰጠው የትምህርት የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ተማሪዎቻቸውን በጊዜው ከጠሩ ዩኒቨርሲቲዎች ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ አንዱ ነው። በዚህም መሰረት ሁለተኛ ዓመትና ከዚያ በላይ የሆኑት መደበኛ ተማሪዎች ወደ ግቢ ገብተዋል። ተማሪዎች የተጠሩትም ዩኒቨርሲቲው ለመማር ማስተማሩ ሂደት አስፈላጊውን ሁሉ ቅድመ ዝግጅት ከተደረገ በኋላ ነው። ተማሪዎች በገቡ ማግስት ወዲያውኑ ትምህርት እንዲጀምሩ ተደርጓል።

የጤና ተማሪዎች ከትምህርት ፕሮግራሙ ጋር በተያያዘ ከአንድ ዓመት ጀምሮ እስከ ሁለት ዓመት ድረስ ትምህርት ተስተጓጉሎብናል ብለው ቅሬታ አቅርበዋል። ለዚህ የዩኒቨርሲቲው ምላሽ ምንድነው? ተብለው የተጠየቁት ዶክተር አክበር፤ የጤና ትምህርት ሲባል በርካታ የትምህርት ክፍሎች አሉትና የትኞቹ ናቸው?። በሚል ጥያቄን በጥያቄ መለሱ። ዝግጅት ክፍሉም ጥያቄውን ግልጽ ለማድረግ ቅሬታ ያነሱት ከሶስተኛ ዓመት ጀምሮ ያሉ የላብራቶሪ፤ የህክምና፤ የፋርማሲ፤ ተማሪዎች ናቸው። ለምሳሌ የሶስተኛ ዓመት ያቀረቡት ቅሬታ ‹‹በዚህ ዓመት አምስተኛ ዓመት መሆን ሲገባን እኛ ግን ያለነው ሶስተኛ ዓመት ላይ ነው። በዚህም አንድ ዓመት ከስድስት ወር በላይ ጊዜ ተቃጥሎብናል›› የሚል ነው ለዚህ ምላሽዎት ምንድን ነው? ተብለው የተጠየቁት ኃላፊው፤ በዩኒቨርሲቲው የተደረገ የፕሮግራም መዛባት የለም። ባለፈው ዓመት ወደ ግቢው ስንመጣ አዲስ ነበርን። ከአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ነው የመጣነው። ባለፈው ዓመት ጥር አካባቢ ሶስተኛ ዓመት ተማሪዎች ክረምቱን ተምረን ማለፍ አለብን ብለው ያመጡት ሃሳብ ነበር። ይሁን እንጂ ጉዳዩን በተግባር ስናጠና ተማሪዎቹ የ2013 የገቡ ተማሪዎች ናቸው። በትምህርት ፕሮግራሙ ላይ ቅሬታ ያላቸው ተማሪዎች በዚያው ዓ.ም የገቡ ተማሪዎች ናቸው። ሌሎች ተማሪዎቸ ላይ ምንም ቅሬታ የለም።

ነገር ግን እነዚህ ተማሪዎች ወደ ዩኒቨርሲቲው የገቡት የትምህርት ዓመቱ ሊያልቅ ሲል ነው። በተጨማሪም በኮቪድ.19 ምክንያት ሴሚስተሩን ሳይጨርሱ ወጡ። ከኮቪድ ጋር ተያይዞ የተዛባው የትምህርት ሴሚስተር የሌሎች ባች ተማሪዎቻችን ጭምር ጎድቷል። ነገር ግን 2013 ዓ.ም ላይ የገቡ ተማሪዎችን የበለጠ ጎድቷል። ምክንያቱም ሰኔ መጨረሻ ላይ ገብተው ሴሚስተር ሳይጨርሱ ቶሎ ወጡ።

ፕሮግራሙ ከዚያ ጀምሮ እንደተዛባ እስካሁን መጥቷል። ስለዚህ ከኮቪድ በተያያዘ የመጣው ችግር በሌሎች ተማሪዎች ላይም ጫና አሳድሯል። የበለጠ ጫና ያሳደረው ግን በ2013 ዓ.ም የገቡ ተማሪዎች ላይ ነው። አሁን ግን በአብዛኛው እየተስተካከለ እየመጣ ነው።

ችግሩ በሚቀጥለው ጥር ወር ሙሉ በሙሉ ይስተካከላል። በተጨማሪም ሰኔ ላይ የሚስተካከል አለ፤ በዚያን ጊዜ ውስጥ ወጥ ይሆናል። ተማሪዎች ባነሱት ቅሬታ ላይ በግልጽ ተወያይተን ያለውን ሁኔታ ለተማሪዎች አስረድተን ችግሩ የመጣው ከኮቪድ ጋር በተያያዘ እንደሆነና ፕሮግራሞች ወደ ፊትና ወደ ኋላ ማለታቸውን በተግባር ተማምነን፤ መቼ የመውጫ ፈተና እንደሚፈተኑ በግልጽ አስቀምጠን አልፈናል። ምናልባት ከጤና ተማሪዎች ጋር በተያያዘ ሌላ ችግር ካለ አይተን ችግሩን እንፈታለን።

‹‹ከዚህ በፊት በነበረው የትምህርት ሥርዓት የጤና ተማሪ ሶስት ወር አርፎ አያውቅም። ውጡ ስንባልም ከገቢው የሚሰጠን ምክንያት አሳማኝና ምክንያታዊ አይደለም። ስንጠይቅም ተገቢነት ያለው ምላሽ አይሰጡንም›› ይላሉና ምላሽዎት ምንድን ነው? የሚል ጥያቄ የተነሳላቸው ምክትል ፕሬዚዳንቱ፤ ከመውጣታቸው በፊት ይህን ዓይነት ቅሬታ ማንሳታቸውን አልሰማንም፤ ከሁሉም የትምህርት ክፍሎች ጋር በጋራ ነው የምንሰራውና ከዚህ ጋር በተያያዘ እምናውቀው ቅሬታ የለም።

ከ2013 ዓ.ም ጋር የተያያዘ ከሆነ ቅሬታው ከኮቪድ ጋር በተፈጠረ መዛባት ነው። ከዚያ ውጭ የህክምና እና ሌላ ጤና ተብሎ ተከፍለው በሚማሩ ተማሪዎች ጉዳይ ለትምህርት ሚኒስቴር ጥያቄ አቅርበን የጤና ትምህርት በተፈጥሮው ለየት ይላልና 11 ወር የሚማሩበት ሁኔታ አለ። ትምህርት ሚኒስቴር ሰርኩላር በጻፈው ደብዳቤ መሰረት መቆየት ያለባቸው ተማሪዎች ግቢ ቆይተው ክረምቱን ሙሉ ተምረዋል። ይህ ከትምህርት ሚኒስቴር አቅጣጫ ውጭ አለመሄዳቸውን ያስረዳሉ።

የህክምና ተማሪዎችን ውጡ አንልም፤ ምክንያቱም እያንዳንዱ ትምህርት የሚመራው በፕሮግራም ነው። ስለዚህ ዓመቱን ሙሉ የሚማሩበት ሁኔታ አለ። እስካሁን ድረስ እየተማሩ ያሉ አሉ። ዲፓርትመንቶች በተለየ መንገድ ትምህርት ጨርሰናል ውጡ ያሉበት ሁኔታ ካለ እናጣራለን። ነገር ግን እኔ እስከማውቀው ድረስና በአሰራር የህክምና ተማሪ ውጡ አይባልም።

የጤናና የላብራቶሪ ተማሪዎች ጊዜ ሳይሰጣቸው ውጡ እንደተባሉ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ነው የወጣነው ይላሉ እና በዚህ ጉዳይ ላይ ምን ይላሉ? የሚል ጥያቄ የተነሳላቸው ዶክተር አክበር፤ ይህን ጉዳይ እናጣራለን። ዋናው ግቢ ከመቶ በላይ ተማሪዎች ሰብሰበን አቅም

> **በተመሳሳይ የትምህርት ክፍል ከእርሱ ጋር ወደ ዩኒቨርሲቲ ገብተው የነበሩ ጓደኞቹ አሁን ላይ ተመርቀው ሥራ ይዘዋል። ይሄንን የተመለከቱ ቤተሰቦቹ አፍ አውጥተው ለምንድነው የማትመረቁት? ተባረህ ወይም ሌላ ችግር ገጥሞህ ከሆነ ንገረን ብለው እንደሚያስጨንቁት ጠቁሟል**

የሌላቸውን ዶርሚታሪ ሰጥተን እንዲቆዩ አድርገናል። ውጡ ብለን ያስወጣናቸው ተማሪዎች የሉም። ነገር ግን ግልጽ መረጃ አጣርተን ተጨማሪ መረጃ መስጠት እንችላለን።

‹‹የፋርማሲ ተማሪዎች ማየት የነበረብን የላብ ውጤቶች እያየን አይደለም፤ ላብራቶሪውም በቂ ግብዓት የለውም፤ ስንጠይቅ በጀት የለም የሚል ምላሽ እየተሰጠን ነው። ማየት ከነበረብን 12 ኬሚካሎች ሁለቱን ብቻ ነው የምናየው ስለዚህ ተመርቀን ብንወጣም ተወዳዳሪ አንሆንም›› የሚሉ ቅሬታዎች ያነሳሉ። ምክትል ፕሬዚዳንቱ፤ የጤና ተማሪዎች የሚማሩት ‹‹ኦቶና›› የጤና ሳይንስ ኮሌጅ ነው።

ዩኒቨርሲቲው ባለው አቅም አስፈላጊው የላብራቶሪ ሙከራ እንዲያዩ እያደረገ ነው። ግብዓት ለማሟላት ጥረት እየተደረገ ነው፤ እናሟላለንም። አንዳንድ ጊዜ ፤ ምናልባትም አልፎ አልፎ ሙብራት ሊጠፉ ይችላልና ሌላ ቦታ ሄደው የሚሰሩበት ሁኔታ እናመቻቻለን። ነገር ግን ያን ያህል ችግር አለ ብለን መናገር አንችልም። መማሪያው ህክምና የሚሰጥበት ሆስፒታል ነው። ታካሚ ሲበዛ በእቅዳችን መሰረት ላይሄድ ይችላል። ነገር ግን ያን ያክል የጎላ ችግር አይደለም።

ለህክምና ተማሪዎች ያላችሁ ትኩረት ምን ያህል ነው? ተብሎ ለተነሳላቸው ጥያቄ ዶክተር አክበር ሲመልሱ፤ ለጤና ተማሪዎች ከፍተኛ ትኩረት እንሰጣለን። ምክንያቱም ጤና ዘርፉ ላይ የሚሰራው በሰው ሕይወት ላይ ነው። ዩኒቨርሲቲው ለዚህ ትልቅ ቦታ አለው። በጤናው ዘረፍ እያከናወነው ያለው ሥራ ለአካባቢው ምሳሌ ሊሆን የሚችል ነው።

ትልልቅ ባለሙያዎች ያሉበት ዩኒቨርሲቲ ነው። የሰው ፍላጎት ሰፊ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን ሁሉንም በአንድ ጊዜ ባናሟላም ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ቅድሚያ በመስጠት ዩኒቨርሲቲው ባለው አቅም ልክ እየሰራ ነው። ስለሆም ለጤና ተማሪዎች የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን አሟልቶ ለማስተማር ጥረት እየተደረገ ነው።

በዚህ ዓመት ለህክምና ትምህርት ምን ያህል በጀት ተመድቦ ምን ያህል ወጪ ተደርጎ የተገዛ ግብዓት አለ? ካለ ቢጠቅሱ? ተብለው የተጠየቁት ኃላፊው በጀት ተመድቦ በሂደት ላይ ነው። ይህ ለህክምና ተማሪዎች ብቻ ሳይሆን በዩኒቨርሲቲው 62 ዓይነት የትምህርት ዓይነቶች አሉ። ለሁሉም እንደ የበጀቱ ግብዓት ለማሟላት ግዥ ሂደት ላይ ነው። የዩኒቨርሲቲው የማስተማሪያ ሆስፒታል ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሕዝብ የሚያስተናግድ ነው። ተማሪዎች ቅሬታ እንዲያቀርቡ የሚያስችል ከባድ ጉዳይ ግን የለም።

ሆስፒታሉ ጠባብ ነው። የማስፋፊያ ሆስፒታል ለመገንባት ታቅዶ እየተሰራ ነው። ሁሉም ተማሪዎች የሚፈልጉት ተሟልቶ ቢማሩ መልካም ነው። ነገር ግን ባለን አቅም እያስተማርን ነው። ከ90 በመቶ በላይ የህክምና ተማሪዎች የመውጫ ፈተናው በማለፍ ወደ ሥራው ዓለም ተቀላቅለዋል። ተምረው የሚመረቁበት ጊዜም ከሌላ ዩኒቨርሲቲ የተለየ አይደለም። በአጠቃላይ ዩኒቨርሲቲው ለተማሪዎች የተሻለ ትምህርትና አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን ዶክተር አክበር ገልጸዋል።

በወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ዋና ዳይሬክተር የሆኑት ዶክተር ወኪል ወልዴ በበኩላቸው፤ ከአንድ ዓመት በላይ የመመረቂያ ጊዜያቸው ያለፈባቸው ተማሪዎች አለመኖራቸውን ገልጸው፤ ባሳለፍነው ዓመት ክረምት ላይ መመረቅ የነበረባቸው ተማሪዎች የመመረቂያ ጊዜያቸው ወደ ጥር መሸጋገሩን ተናግረዋል።

ጊዜውም የተገፋበት ምክንያት በዩኒቨርሲቲው የሚፈተኑ የ12ተኛ ክፍል ተማሪዎች በመኖራቸው እና በሰላም ሚኒስቴር የሚሰለጥኑ ሰልጣኞች በግቢው ውስጥ ስለነበሩ ነው። በ2012 ዓ.ም የ12ተኛ ክፍል ተፈታኝ መሆን የነበረባቸው ተማሪዎች በኮቪድ ምክንያት አንድ ዓመት ወደኋላ ቀርተዋል። ይሄንን ለማካካስ እንደ ሀገር አግባብነት ባለው አካሄድ እየሄድን ነው። ከትምህርት ሚኒስቴር በመጣው መርሃ ግብር መሰረት የጤና ተማሪ ከሆነ በዓመት ውስጥ 10 ወራት የህክምና ተማሪዎች ደግሞ 11 ወራት ነው የሚማሩት።

የፋርማሲ ተማሪዎች በላብራቶሪ ኬሚካሎች አለመሟላት የተግባር ትምህርት በተገቢው መንገድ መከታተል አልቻልንም ይላሉ ስንል ላነሳንላቸው ጥያቄ የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል።

‹‹ለፋርማሲ ተማሪዎች የተገዙ ኬሚካሎችን ሲጠቀሙ ቆይተዋል። ነገር ግን አሁንም ቢሆን አንዳንድ ያልተሟሉ ሊኖሩ ይችላሉ። በሀገር አቀፍ ደረጃ እንዲገዙ ጥያቄ አቅርበናል። አንዳንዶቹ ገበያ ላይ ባለመገኘታቸው ሌሎቹ ደግሞ በበጀት መጓደል ያልተሟሉ አሉ። ይህ ሲባል ግን ተግባር ትምህርትን ለመከታተል የሚዳግቱ ግን አይደሉም። ››

በተጨማሪም 170 የሚሆኑ የህክምና ተማሪዎችም በዋናው ግቢ መኖራቸውን ገልጸው፤ ወደ ኮሌጁ መተው የሚማሩበትን ሁኔታ ለማመቻቸት የዶርሚተሪ ማስተካከል ሥራዎች መጀመራቸውን ተናግረዋል።

ከመጸዳጃ ቤት እና ከመታጠቢያ ቤት ጋር ተያይዞም በኮሌጁ ውስጥ ሶስት የተማሪ ማደሪያ ህንጻዎች አሉ። ከሶስቱ አንዱ ህንጻ የውሃ ፍሳሽ ችግር አለበት ። ይሄንን ከህንጻ ተቋራጮች ጋር ተነጋግረን በከፊል ዘግተነዋል። የውሃ ፓንፑም ተበላሽቶ ነበር። አሁን ግን ፓንፑን አስተካክለን ውሃ ወደ ህንጻው እንዲወጣ እያደረጉ መሆኑን ገልጸዋል።

የተበላሹ ቁም ሳጥኖችን ‹‹ሎከሮችን›› ለማስጠገን እና የአዳዲስ ግዥ ለመፈጸም ከማኔጅመንት ጋር ንግግር ተደርጓል። የግዥ ሂደቱ ግን በዚህ ቀን ተጠናቆ ለተማሪ ይደርሳል ማለት አይቻልም። ከጋዋን ጋር የሚነሱ ጥያቄዎችን ለመፍታት በሂደት ላይ መሆናቸውን እና በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለተማሪዎች እንደሚደርስ ገልጸዋል።

# የደራው የልመና ገበያ!

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

ዓይን ሲያይ ልብ ይፈርዳል። የተመለከትነውን ተመልክተን የሰማነውንም ሰምተናል። ነገር ግን ግብር የማይጣልበት፣ ቀረጥ የማይቀረጥበት አዲስ የሥራ መስክ ያለ ምንም የንግድ ፈቃድ ስለመምጣቱ ያስተዋልን ግን ስንቶቻችን ነን? ብቻዬን ተመልክቼ ብቻዬን የምፈርድ እንደሆን በመፍረዴ ይፈረድብኛልና ጥቂት ስለ ሀቁ አስበን ስለመፍትሔው ብናሰላስል ይሻላል ባይ ነኝ።

ከብጣሽ ጽሑፌ መግቢያ እስከ መደምደሚያ የማውራት ፍላጎቴ አጥተው ነጥተው ስለሚለምኑት የኔ ቢጤዎች ሳይሆን በሌላኛው አቅጣጫ ልመናን እንደ አዲስ ቢዝነስ የአጭርና የረዥም ጊዜ ዕቅድ ነድፈው እየሠሩበት ስላሉት ነውረኞች ነው። የትም ሳንሄድ፤ አዲስ አበባ የአፍሪካ ብቻ ሳትሆን የለማኞች መዲናም ጭምር ሆናለች።

በአዲስ አበባ ጎዳናዎች ላይ በእግር ከመራመድ በላይ የሚያደክመውና የሚያስጨንቀው ከዚም ከዚያም ከሚታዩት የሚሰማው የሰለሉ የልመና ድምጾች ናቸው። አሁን አሁን ከንፈር ከመምጠጥ የልብ ስብራት ወደ ጥያቄ አጫሪነት ተሸጋግሯል። ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ባልተለመደ መልኩ እንደ አሸን እየፈሉ፤ ከመጽዋቹ ተመጽዋቹ ለመብለጥ የቀረው የለም። ልመና ሳይሆን የልመና ፌስቲቫል የሚካሄድ መስሎ ሲታይ ከዚህ በላይ ሊያሳስበን የሚገባ ምን አለ?

ምንዱባን፣ የጎዳና ሰው፣ የኔ ቢጤ በየትኛውም የሠለጠኑና ሀብታም ሀገሮች ውስጥ ያለና የሚኖር ነው። በሀገራችንም የተቸገረውን መርዳት ለዘመናት የቆየው ባሕላችን ነው። እኛ ጣል አድርገናት የምናልፋት ሳንቲም ለኛ በረከትን ስለማምጣቷ እንጂ ከበስተጀርባዋ ያላትን አንመለከትም።

ከተባረኩበት ማንም ይሁን ለማን እኔ ምን አገባኝ እሳቤያችንን ለጽድቅ ሳይሆን ለኩነኔ እየተደረገብን ነው። ምጽዋት የሚገባቸው ምስኪኖች ዳር ላይ ተረስተው በሌላ የበግ ለምድ በለበሱ ምንደኞች ተሸፍነዋል። ዞረን ለምዱን ብንገልጥ በየርምጃው የተሰገሰጉ ተኩላዎች ለጉድ ናቸው።

የበጎቹን ሳር ቅጠል የሚለቅሙትን እኚህን ተኩላዎች መንጥሮ ርምጃ መውሰዱ የሕግ አካላት የቤት ሥራ ሊሆን አይገባም ወይ? አስመሳዮች የሚያደርጉትን ተመልክቶ፤ በሞት አፋፍ ቆሞ የርዳታ ጥሪውን ሲያስተጋባ "ውሸታም!" ብሎ ማለፍ የጀመረው ማህበረሰብስ በአረሙ ምክንያት አዝመራውን ረግጦ ማለፉ ተመችቶት ይሆን? አይመስለኝም። ሁላችንም መፍትሔውን እንፈልጋለን። ግን ሰጪና አምጪው ማነው? ከእኛ ሌላ ማንስ ይምጣ?

በፊት በፊት በልመና ውስጥ የምንመለከታቸው ጧሪ ደጋፊ ያጡ፣ ወላጅ አልባ፣ የአካል ጉዳተኛ፣ ለሥራ አቅምና አካል አጥተው በችጋር ሳማ የተገረፉ ነበሩ። ሀፍረት ተከናንበው አማራጭ ስላጡ ብቻ የሚገቡበት ነበር። ዘንድሮ ግን ልመና የእነዚህ ብቻ አይደለም። ጠብ ለማይል ኑሮ ሠርቶ ከእጅ ወደ አፍ ከማለት ልመናው አዋጭ የሥራ ዘርፍ መሆኑን ተመልክተው ያለ ሀፍረት በጥበብ የገቡበት ቁጥር የላቸውም።

አሳፋሪ የነበረው ልመና ያለ ድካም የሚያበላና ዓይን የማይታሽበት ተደርጎ ከዘመኑ ጋር አዘምነውታል። መለስ ብለን ካስተዋልን በሴተኛ አዳሪነት የነበረው ታሪክ ነው። አማራጭ በማጣት ካለመሞት መሰንበት ተብሎ የሚገባበት

> **ከ**ቅርብ ዓመታት በፊት በገጠሩ የሀገራችን ክፍል የሚኖረው ማህበረሰብ እንደ ልመና አምርሮ የሚጠላውና እንደ አሳፋሪ የሚያየው ነገር አልነበረም። ‹‹ነፍሴ እያለች…›› እያለ ልመናን አምርሮ የሚጸየፍ ነበር። ‹‹ሰው እንዴት ሙሉ አካል ይዞ ይለምናል?›› እያለ የሚገረም ነበር። አብዛኛው የገጠር ሥራ ከአካላዊ ጤንነት ጋር የሚያያዝ የጉልበት ሥራ በመሆኑ ጤንነት አስካለው ድረስ ልመናን አያስበውም። ለሱ ጤነኛ ሆኖ መለመን እጅግ በጣም ነውር ነበር

አስነዋሪ ተግባር ነበር። ቆይቶ ግን ከተማሪ እስከ ዕውቅ ቆነጃጅት በደላሎች እየተመለመሉ ዘመናይ ሴተኛ አዳሪዎች ተፈጠሩ። ከባለገንዘቦች ጭን ስር መገኘት፤ ደህና ሰንብት ድህነት ተብሎ የሀብት ቁልፍ መረካከቢያ አደባባይ ሆነ። ዛሬ የምንመለከተውም ይኼው ነው። ዳግም በልመናው ታሪክ እየተደገመ ነው።

ዛሬ ላይ በየአደባባዩ በምንመለከተው በደራው የልመና ገበያ ውስጥ መሆን ሳይሆን መስሎ መታየት ትልቁ ጥበብ ነው። በፊልም ኢንዱስትሪው ውስጥ እንኳን ያልተመለከትነውን የትወናና የሜካፕ ጥበብ በልመናው ውስጥ እየተመለከትን ነው። እንኳን አዋቂው ሕፃናቱ ሳይቀር በደህና ደራሲ ተቀርጸው፣ በድንቅ ዳይሬክተር በመመራት አጃኢብ ነው! የሚያስብል የትወና ብቃታቸውን ያሳያሉ።

የተሰረቁና መሰል ሕፃናትን በየጎዳናው ላይ የሚያሰማሩ የበስተጀርባ ዘዋሪዎች ቀድሞም የነበሩ ቢሆንም አሁን ግን ከዘመኑ ጋር አዘምነው እረቀቅ አድርገውታል። ውስጡን ብንፈትሽ፤ በዝርፊያው ዓለም ውስጥ ከአሸባሪ ባልተናነሰ የተደራጁ የማፍያ ቡድኖች እንዳሉ ሁሉ ከልመናውም በስተጀርባ ፈርጣማ ቡድኖችን መቆም ጀምረዋል።

ከዝርፊያው የሚለየው በበጎ ፈቃድ ላይ የተመሠረተ ሰላማዊ ዘረፋ መሆኑ ብቻ ነው። የታማሚን ምስልና ማሞኛ ቃላትን የያዙ ትልልቅ ባነሮች ይሠራሉ። የኪራይ መኪና የኪራይ ጀነሬተር ይዘጋጃል። ስፒከር ተሰቅሎ ድምጽ ማጉያ ይጨበጣል። አንጀት መብያ የመለመኛ ሙዚቃና ክላሲካሎች ከፍ ተደርገው ይደመጣሉ።

ከሆድ አደር የህክምና ባለሙያዎችና ተቋማት የውሸት ማስረጃዎችን በማጻፍ ይለጣጠፋሉ። በጥሩ ሜካፕ አርቲስት የተሠራው ተዋናይ በመርሀ ተውኔቱ እየተመራ ይተውናል። እንግዲህ ሙዚቃዊ ተውኔት መሆኑ ነው። ከዚህ ቀደም በመርካቶና በሌሎች ጥቂት በማይባሉ ስፍራዎች በጥቆማ የተያዙት ለዚህ ማሳያ ናቸው። ይሄም ከብዙ የልመና ስልቶች መካከል አንደኛው እንጂ ብቸኛው አይደለም። በግልና በቡድን ሌላውም ዓይነት ይቀጥላል።

የልመናውን አዋጭነት በማመን ከሥራ አምልጠው የገቡ ሁሉ ምክንያታቸው የተትረፈረፈ ብልጽግናን ፈልገው አይደለም። ራሳቸውን ለማኖር ሥራ ያጡ ይሆናሉ። ሥራ ቢኖራቸውም ገቢያቸው የማያኖራቸው ሆኖ ያገኙታል። የያዘ ይዞት እንጂ በልመናው ጠንክሮ ከማንም የወር ደመወዝተኛ የተሻለ ገቢ የሚያገኝ እንዳለ አይካድም።

በወሬም ይሁን በእውን እሱ የሚመጸውተው ተመጽዋች ከእርሱ የተሻለ እንደሚያገኝ ያሰበበት ዕለት ብድግ ብሎ ከሥራው ልመናውን ይመርጣል። በኛ በሦስተኛው ዓለም ውስጥ ርካሹ ነገር ጉልበት ነው። አብዛኛው ሕዝብ ደግሞ ጥሮ ግሮ የሚኖረው በጉልበቱ ነው። ይኼው ትኩስ ኃይልና ጉልበትም ራሱን ለማኖር ሲል በተስፋ መቁረጥ የልመናውን ቢዝነስ ይቀላቀላል።

ችግሩ ያለው ልመናው ላይ ሳይሆን የሚሠራው የሰው ኃይል በመቀነሱ በተዘዋዋሪ ሀገር የምታጣው ብዙ መሆኑ ነው። ኢኮኖሚው ለሁሉም በቂ እንዲሆን ሁሉም መሥራት ይኖርበታል። የሚለምነው በዛ ማለት የአንዱን ሰው ገቢ ለሁለትና ለሦስት እየተሻማንበት ነው ማለት ነው። ሳይሠራ ቁጭ ብሎ ገንዘብ የሚሰበስበው ግለሰብ እያገኘ ነው ብንልም፤ በኢኮኖሚ እሳቤ ግን ከግለሰቡ ገቢ በብዙ እጥፍ ሀገር እያጣች ነው እንደማለት ነው።

ስለዚህ የደራው የልመና ገበያ ውስጥ ወንጀል ብቻ ሳይሆን ትልቅ የኢኮኖሚ ማገርም ጭምር እየተመዘዘ ነው። የእውነትም ተቸግረውም ይሁን ታዘው ምንም የማያውቁ ሕፃናት ፊደል በመቁጠሪያ ዕድሜያቸው የልመናን ሀሁ ያጠናሉ። ምንም ሳያውቁ በፊት ነጭ ወረቀት የመሰለው ጭንቅላታቸው በልመና ተቀርጾ ነገ ላይ ምን ወርቅ ብናነጥፍላቸው ነገ ላይ ምን ዓይነት ትውልድ ነው የሚሆኑት? በልመና የታሸ ትውልድ ይዘን የምንገነባት ሀገርስ የነገው መልኳ ምን መሳይ ይሆን?

ከቅርብ ዓመታት በፊት በገጠሩ የሀገራችን ክፍል የሚኖረው ማህበረሰብ እንደ ልመና አምርሮ የሚጠላውና እንደ አሳፋሪ የሚያየው ነገር አልነበረም። ‹‹ነፍሴ እያለች…›› እያለ ልመናን አምርሮ የሚጸየፍ ነበር።

‹‹ሰው እንዴት ሙሉ አካል ይዞ ይለምናል?›› እያለ የሚገረም ነበር። አብዛኛው የገጠር ሥራ ከአካላዊ ጤንነት ጋር የሚያያዝ የጉልበት ሥራ በመሆኑ ጤንነት አስካለው ድረስ ልመናን አያስበውም። ለሱ ጤነኛ ሆኖ መለመን እጅግ በጣም ነውር ነበር።

የችግሩ ክፋት ደግሞ ሕፃናት እና ታዳጊዎች ልመናን እንደ አንድ የሥራ ዘርፍ እያዩት እና እየተቀበሉት መሄዳቸው ነው። አሁን አሁን በየመንገዱ ሕፃናት ልጆች የአዋቂዎችን ልብስ እየያዙ ሲለምኑ ማየት ተለምዷል። እነዚህ ሕፃናት ከወላጆቻቸው ጋር እየለመኑ ነው። የልመናን ነውርነት እየሰሙ ሳይሆን እንደ ሥራ እያዩት እያደጉ ነው። የነዚህ ሕፃናት ልጆች ቀጣይ እጣ ፈንታ ምን ሊሆን እንደሚችል ማሰብ አይቸግርም።

ችግሩ አሁን ባለበት ደረጃ እየቀጠለ ከሄደ እንደ ሀገር ሊፈጥረው የሚችለው አደጋ የቱን ያህል የገዘፈ ሊሆን እንደሚሆን መገመት አይከብድም፤ የከተሞች መንገድ ብቻ ሳይሆን ገጠሮቻችንም በተመሳሳይ መልኩ ልመናን ሥራ ባደረጉ ዜጎች መሞላታቸው የማይቀር ነው ።


ምጽዋት ሸቶ የወጣውን አትለምንም ተብሎ ሊከለከል አይችልም። ለደራው ገበያ የሥራ ፈቃድ አውጣ ልንለው አንችልም። የውሸቱን ይሆናል ብለን ምጽዋታችንን ሳንሰጥ ስለማለፍም ማሰብ የለብንም። ተኩላውን ከበጎቹ መለየት አንዱ መፍትሄ ቢሆንም፤ በዚህ ወንጀልን እንከላከል ይሆናል እንጂ ለችግረኛው ዘላቂ መፍትሔ አይሆንም።

ምጽዋታችንን ከኪስ አውጥተን ጣል ማድረጋችን መልካም ቢሆንም በቂ ግን አይደለም። መንግሥት እንደ መንግሥት የሥራ ዕድሎችን ከጥሩ ገቢ ጋር ለመፍጠር መሥራት ይኖርበታል። የኑሮ ውድነቱን በመቆጣጠር ከዜጎች ገቢ ጋር መሳ ለመሳ የሚሄድ ማድረግ ግድ ነው።

በችግር ለወደቁ ሕፃናትና አረጋውያን እንዲሁም አካል ጉዳተኞች ትኩረት በመስጠት ከጊዜያዊነት ያለፈ ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋል። ከሀገር በቀልም ሆነ ከውጭ የርዳታ ተቋማት ጋር አብሮ በመሥራት የወደቀውን ማንሳት መረሳት የለበትም። ችግሩ ላይ ብቻ ከማተኮር ወደኋላ ምንጩን ለማድረቅ ባንጠራራ እንኳን ለመቀነስ መሥራት ነው። አሳሳቢውን የደራ ገበያ ማጥራቱ ግን፤ ፋታ የማያሰጠው ወሳኝ ጉዳይ ነው።

# የኢኮኖሚው ደጀንነቱን ማረጋገጡን የቀጠለው ቡና

**ፍሬሕይወት አወቀ**



የቡና መገኛ በመሆኗ የምትታወቀው ኢትዮጵያ በቡና ምርቷም በእጅጉ ከሚታወቁ ሀገራት ተርታም ትሰለፋለች። ቡና በሀገሪቱ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥም ጉልህ ስፍራ እንዳለው ይታወቃል። በርካታ አርሶ አደሮች፣ ነጋዴዎችና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎችም የሚሳተፉበት ዘርፍ ከመሆኑ በተጨማሪ ለሀገሪቱ የውጭ ምንዛሬ በማስገኘት ከሚጠቀሱት የግብርና ምርቶች መካከልም ግንባር ቀደም በመሆንም ይታወቃል።

ሀገሪቱ በቡና የመታወቋን ያህል ተጠቃሚ ሆናለች ወይ ተብሎ ሲጠየቅ ግን መልሱ የሚገባትን ያህል ተጠቃሚ አይደለችም የሚል ይሆናል። ለዚህም ምክንያቶቹ ዘርፈ ብዙ ስለመሆናቸው መረጃዎች ያመላክታሉ።

እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የግብይት ሰንሰለቱ የተንዛዛ ሆኖ መኖሩ አንዱና ዋነኛው የዘርፉ ችግር በመሆን ሲጠቀስ ቆይቷል፤ ግብይቱ በደላላ የተተበተበ ሆኖ ኖሯል። መሰረታዊ የጥራት ችግርም እንዲሁ ሌላው የዘርፉ ተግዳሮት ነበር። በዚህ የተነሳም ለውጭ ገበያ ይቀርብ ከነበረው ቡና አብዛኛው ኮሜርሻል ቡና የነበረ ሲሆን፣ የስፔሻሊቲ ቡና አቅርቦት መጠን ያነሰ ነበር። ቡናውን ለዘመናት ለውጭ ገበያ ያቀርቡ የነበሩት የተወሰኑ ነጋዴዎች ብቻ እንደነበሩና ይህም የዘርፉ አንዱ ችግር እንደነበር መረጃዎች ያሳያሉ።

እነዚህንና መሰል የዘርፉን ችግሮች ለመፍታት የቡናና ሻይ ባለስልጣን የሪፎርም ሥራ ሰርቷል። ይህን ተከትሎም ባለፉት አምስት ዓመታት በቡና ላይ በብዙ መልኩ ለውጥ ማምጣት ተችሏል። በተለይም በቡና ግብይትና ጥራት ችግር ላይ ይስተዋሉ የነበሩና ስር የሰደዱ ችግሮችን በወሳኝ መልኩ መፍታት የተቻለበት ሁኔታ ተፈጥሯል።

እነዚህ የሪፎርም ሥራዎች የተንዛዛውን የቡና ግብይት ሰንሰለት ማሳጠር ተችሏል፤ ቡና ለውጭ ገበያ የማቅረቡ ሥራ ለዘመናት በተወሰኑ ላኪዎች ቁጥጥር ስር የነበረበትን ሁኔታ በመቀየር አርሶ አደሩን ጨምሮ ሌሎች አካላትም ላኪ መሆን የሚችሉበት አሰራር ተፈጥሯል። በተለይ የቡና የቀጥታ ግብይት ሥርዓት ተግባራዊ መሆን በዘርፉ ለተገኘው ለውጥ ትልቅ አስተዋጽኦ ማበርከቱ ይገለጻል።

የቡና ጥራትን በማረጋገጥ በዓለም አቀፍ የቡና ገበያ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ማስገኘት የሚያስችለውን የስፔሻሊቲ ቡና መጠን የመጨመር ሥራ ተሰርቷል። በዚህም ከኮሜርሻል ቡና ብልጫ ያለው ስፔሻሊቲ ቡና ለውጭ ገበያ ማቅረብ ተችሏል። ባለሥልጣኑ የገበያ መዳረሻዎችን በማስፋት፣ ጥራቱን በማስጠበቅና ያረጁ የቡና ተክሎችን በመጎንደል፣ አዳዲስ የቡና ችግኞችን በመትከል በቡና ልማት ላይም በትኩረት ሰርቷል።

የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን «ቡናችን ለብልጽግናችን በሚል» መሪ ሃሳብ ባዘጋጀው መድረክ በብሔራዊ ሳይንስ ሙዚየም በቅርቡ ባካሄደው መድረክ ላይም በዘርፉ በርካታ ስኬቶች መመዝገባቸው ተጠቅሷል። የዚህ መድረክ ዋነኛ ዓላማ ለቡናው ዘርፍ ለደረሰበት ስኬት አስተዋጽኦ ያደረጉ ጀግና አርሶ አደሮች፣ ላኪዎች እና ሌሎች የዘርፉ ተዋንያን ላበረከቱት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ዕውቅና ተሰጥቷል።

እውቅና ከተሰጣቸው ዘርፎች መካከልም ቡናቸውን በከፍተኛ ጥራት ያመረቱ፣ ቡናቸውን አምርተው በቀጥታ ለውጭ ገበያ ማቅረብ የቻሉ በመጠን ከፍተኛ የሆነ የቡና ምርት ወደ ውጭ የላኩ፣ በከፍተኛ ዋጋ ቡናቸውን ለውጭ ገበያ መሸጥ የቻሉ እንዲሁም በሌሎችም የተለያዩ ዘርፎች ውጤት ያስመዘገቡ አካላት ይገኙበታል። እነዚህ የቡና ቤተሰቦችም በየደረጃው ተሸልመዋል።

በመድረኩ የተገኙት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ፤ ባለፉት አምስት ዓመታዊ የቡና ምርት መጠንን ከነበረበት 500 ሺህ ቶን በእጥፍ ማሳደግ እንደተቻለ ገልጸው፤ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያውን ተከትሎ ባለፉት ሁለት ወራት ከቡና ወጪ ንግድ ከቀደሙት ዓመታት ከፍተኛ ብልጫ ያለው ገቢ መገኘቱንም ተናግረዋል። ባለፉት አምስት ዓመታት ለቡና ምርትና ጥራት መጨመር ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ መሰራቱን አመልክተው፣ በተለይ በቡና ችግኝ ተከላና ጉንደላ ላይ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት መሰራቱን አስታውቀዋል።

በዚህም የኢትዮጵያ ዓመታዊ የቡና ምርት መጠንን ከአምስት ዓመታት በፊት ከነበረበት 500 ሺህ ቶን ወደ አንድ ሚሊዮን ቶን ማሳደግ ተችሏል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ከገቢ አንጻርም እንዲሁ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ኢትዮጵያ ከቡና ወጪ ንግድ ከአንድ ነጥብ አራት ቢሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ማግኘቷን አስታውቀዋል። በተያዘው በጀት ዓመት ይህን አሃዝ ወደ ሁለት ቢሊዮን ዶላር ከፍ ለማድረግ ታቅዶ እየተሰራ እንደሆነ ጠቁመዋል።

ኢትዮጵያ የቡና መገኛ ብቻ ሳትሆን የዓለም ከፍተኛ ቡና አምራች ከሆኑ ሀገራት መካከል አንዷ እንድትሆን ለማድረግ የተጀመሩ ሥራዎች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ ያስታወቁት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ይህን እውን ለማድረግ ከመንግሥት በተጨማሪ ላኪዎች የቡና ምርት ጥራትን ለሚያሻሽሉ ተግባራት ኢንቨስት ማድረግ እንዳለባቸው አስገንዝበዋል። ላኪዎች በቡና ምርት ላይ ውበት ያለው አስተሻሸግ ዘዴ በመጠቀም እሴት ጨምረው ለወጪ ገበያ ማቅረብ ላይ ትኩረት ማድረግ እንዳለባቸውም ጠቁመዋል።

የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ኢትዮጵያ በሁሉም መስክ በዓለም ገበያ ይበልጥ እንድትሳተፍ እንደሚያደርጋት የገለጹት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ማሻሻያውን ተከትሎ ባለፉት ሁለት ወራት ከቡና ወጪ ንግድ ከቀደሙት ዓመታት ከፍተኛ ብልጫ ያለው ገቢ መገኘቱን ገልጸዋል። «በቀጣይም የሚገጥሙ ፈተናዎች ሳያቆሙን በሁሉም መስክ የኢትዮጵያን ብልጽግና እውን ለማድረግ እንሰራለን» በማለት አጽንኦት ሰጥተው ተናግረዋል።

የግብርና ሚኒስትር ግርማ አመንቴ (ዶ/ር)፤ «ግብርናችን ከእጅ ወደ አፍ መሆኑ ቀርቶ አሁን ላይ ወደ ውጭ ምርቶችን በማቅረብ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነታችንን ማሳደግ ተችሏል» ሲሉ ጠቅሰው፣ የቡና ሽያጭ አማራጭ እንዲሰፋ በመደረጉ እና አርሶ አደሮች የቡና ምርታቸውን የላኪነት ፍቃድ አግኝተው ወደ ውጭ ገበያ እንዲያቀርቡ ማድረግ በመቻሉ በዘርፉ አበረታች ውጤት መመዝገብ ችሏል ሲሉ ገልጸዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ በዘርፉ በተሰራው የሪፎርም ሥራ ከአንድ ሺህ በላይ አርሶ አደሮች የቡና ምርታቸውን በቀጥታ ለውጭ ገበያ ማቅረብ ችለዋል፤ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በርካታ ሥራዎች ተሰርተዋል። በዚህም ባለፉት ስድስት ዓመታት በሀገር አቀፍ ደረጃ ስምንት ነጥብ አምስት ቢሊየን አዳዲስ የቡና ችግኞች ተተክለዋል፤ የኢትዮጵያ የቡና ልማት ጥራትና ምርታማነቱ አድጎ የውጭ ምንዛሬ ግኝቱም ከፍተኛ ጭማሬ እያሳየ መጥቷል።

በአምራች አርሶ አደሮች አንድ ኪሎ ግራም ባለ ልዩ ጣዕም ቡና ከ100 ሺህ ብር በላይ እየተሸጠ መሆኑን ሚኒስትሩ ጠቅሰው፣ ከቡና የእሴት ሰንሰለት የሚያገኙት ድርሻም እያደገ መምጣቱን ተናግረዋል። ኢትዮጵያ በአፍሪካ ግንባር ቀደም በዓለም ደግሞ ሦስተኛ የቡና አምራች ሀገር በመሆን በተወዳዳሪነት መጠቀሷን ገልጸዋል። ኢትዮጵያ የጂ-25 ቡና አምራች ሀገራትን በሊቀ መንበርነት በመምራት ላይ እንደምትገኝ ተናግረው፣ ቡና የአፍሪካ 2063 ስትራቴጂክ የንግድ ምርት ሆኖ እንዲሰየም ለሕብረቱ ጉባዔ ያቀረበችው ጥያቄም ተቀባይነት ማግኘቱን አመላክተዋል። ይህም መሠረት በአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣና የትግበራ ሂደት በቀዳሚነት ወደ ግብይት ከሚገቡ ምርቶች መካከል ቡናን ቀዳሚ እንደሚያደርገው ሚኒስትሩ ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አዱኛ ደበላ ከመድረኩ አስቀድሞ በሰጧቸው መግለጫዎች ቡና ካለፉት አምስት ዓመታት ወዲህ ውጤት እያስመዘገበ መሆኑን አስታውቀዋል። ቡና ለሀገሪቱ ኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት የመሪነቱን ሚና የሚጫወት ወሳኝ የግብርና ምርት መሆኑን ጠቅሰው፣ ለሀገሪቱ የብልጽግና ጉዞ መሳካት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው አመልክተዋል።

መንግሥት የቡና ምርትና ምርታማነትን በመጨመርና ጥራቱን በማሻሻል በዓለም ገበያ ተፎካካሪነቱን የበለጠ በማሳደግ ኢኮኖሚያዊ መዋቅራዊ ሽግግሩን ዕውን ለማድረጉ ሂደት አስተዋጽኦ ማበርከት እንዲችል ከፍተኛ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል ሲሉም ጠቅሰው፣ በዚህም አበረታች ውጤቶችን ማስመዝገብ መቻሉን ዋና ዳይሬክተሩ ተናግረዋል።

ዋና ዳይሬክተሩ እንዳሉት፤ ኢትዮጵያ የቡናን ምርት ለዓለም ገበያ ማቅረብ ከጀመረችበት ጊዜ አንስቶ ፍጹም ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ባለፈው በጀት ዓመት 300 ሺህ ቶን ቡና ለውጭ ገበያ ቀርቦ አንድ ነጥብ 43 ቢሊየን ዶላር ተገኝቷል። ካለፉት አራት ዓመታት ወዲህ በዘርፉ አበረታች ውጤት እየተመዘገበ መጥቷል። ለዚህም ስኬት መመዝገብ መንግሥት ለዘርፉ የሰጠው ትልቅ ትኩረት አንዱ ሲሆን፤ ባለሥልጣኑ የሰራቸው የሪፎርም ሥራዎችም በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው።

ወደ ውጭ የሚላከውን የኮሜርሻል ቡና መጠን በመቀነስ የስፔሻሊቲ ቡናን መጠን ከፍ ለማድረግ ዕቅድ ተይዞ መሰራቱን ዋና ዳይሬክተሩ ጠቅሰው፣ በዚህም ውጤት ማምጣት እንደተቻለ አስታውቀዋል። የዛሬ ሶስት ዓመት የኮሜርሻል ቡና መጠን በመቶኛ ሲታይ 70 በመቶውን ይሸፍን እንደነበር አስታውሰው፣ የስፔሻሊቲ ቡና መጠን ደግሞ 30 በመቶ እንደነበር ዋና ዳይሬክተሩ አመልክተዋል። ዛሬ ላይ ግን የስፔሻሊቲ ቡናን ከፍ በማድረግ 60 በመቶ ማድረስ እንደተቻለና የኮሜርሻሉን ደግሞ ወደ 40 በመቶ ማውረድ መቻሉን ገልጸዋል።

ባለሥልጣኑ ከቡና ልማት ጀምሮ ቡናውን ለውጭ ገበያ /ኤክስፖርት/ ማቅረብና ገበያ ማስፋፋት ድረስ ትርጉም ያለው ሥራ እየሰራ መሆኑን አመልክተው፣ በተለይም የእሴት ሰንሰለቱን በመከተል ልማቱ እንዲጨምርና ምርትና ምርታማነት እንዲያድግ የገበያ መዳረሻዎች እንዲሰፉና የውጭ ምንዛሪ ግኝቱ እንዲያድግ በተደረገው ጥረት ውጤት መመዝገቡን ተናግረዋል። የምርት ጥራትን በማስጠበቅና ብክነትን በመከላከል እንዲሁም በእሴት ጭመራ ላይ በተከናወኑ ተግባሮች ለውጭ ገበያ የሚቀርበውን ቡና መጠን ማሳደግና ከቡናውም የሚገኘው የወጪ ምንዛሪ መጠን እያደገ እንዲመጣ ማድረግ መቻሉን አስታውቀዋል።

ባለሥልጣኑ ዘርፉን ውጤታማ ለማድረግ በዋናነት ከሰራቸው ሥራዎች መካከል ግብይቱን አንቀው የያዙና ልማቱ ውስጥ የሚገኙ እንዲሁም ግብይት ውስጥ ያሉና ልማቱ እንዳይስፋፉ ያደረጉ ችግሮችን ነቅሶ ማውጣት አንዱ መሆኑን አመልክተው፣ ለዚህም የ15 ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ በማዘጋጀት በዋናነት ስድስት የተለያዩ ምሰሶዎችን በመለየት ልማትና ግብይቱን የማሳደግ ተግባሮች መከናወናቸውን አስታውቀዋል። ምርትና ምርታማነት ከፍ እንዲል፣ የምርት ጥራት እንዲጨምርና ዘርፉ በምርምር እንዲደገፍ፣ የእሴት ሰንሰለቱን የማሳጠር፣ በምርቱ ላይ እሴት ጨምሮ ለገበያ ማቅረብ እንዲሁም ገበያን የማስፋፋት ሥራ በስፋት መሰራቱንና አሁንም እየተሰራ መሆኑን አስታውቀዋል።

ባለሥልጣኑ ባደረገው ሪፎርም በተለይም የቡናው ዘርፉ ከዓመት ዓመት የተሻለ ውጤትና ስኬት እያስመዘገበ መሆኑን ዋና ዳይሬክተሩ ይጠቅሳሉ። ወደ ውጭ የሚላኩ የቡና፣ የሻይና የቅመማ ቅመም ምርቶች በመጠን እየጨመሩ፣ ከእነዚህ ምርቶች የሚገኘው የውጭ ምንዛሪ ግኝትም በየዓመቱ እያደገ መምጣቱን ተናግረዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ በ2016 በጀት ዓመት ኢትዮጵያ 300ሺ. ቶን ቡና ወደ ውጭ ገበያ በመላክ ከአንድ ነጥብ አራት ቢሊዮን በላይ የአሜሪካ ዶላር ገቢ ማግኘት ችላለች። ይህ ውጤትና ስኬት የተመዘገበው ብዙ ጥረትን በጠየቀው የሪፎርሙ ሥራ ነው። ሪፎርሙ ተግባራዊ ከመደረጉ አስቀድሞ ከ180 እስከ 190 ሺ. ቶን ቡና ብቻ ለውጭ ገበያ ይላክ የነበረ ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅት እስከ 300 ሺ. ቶን ቡና ለውጭ ገበያ ማቅረብ ተችሏል። በአጭር ጊዜ ውስጥ መቶ ሺ. ቶን የተጣራ ቅሽር ቡና ለውጭ ገበያ በሚላከው ቡና ላይ መጨመር የተቻለ ሲሆን፣ ይህም ዘርፉ የእሴት ሰንሰለቱን በማሳጠር ያስመዘገበው ትልቅ ስኬት ነው።

ባለሥልጣኑ ለ2017 በጀት ዓመት ጥራት ያለውና በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ መሆን የሚችል ቡና በከፍተኛ መጠን የመላክ ዕቅድ ይዞ እየሰራ መሆኑንም ዋና ዳይሬክተሩ አስታውቀዋል። በ2016 በጀት ዓመት ሶስት መቶ ሺ. ቶን ቡና ለዓለም ገበያ በመላክ ከተመዘገበው ከአንድ ነጥብ አራት ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር በላይ ገቢ ከፍ በማድረግ፣ በ2017 በጀት ዓመት 326 /ሶስት መቶ ሃያ ስድስት/ ሺ. ቶን ቡና ለዓለም ገበያ በማቅረብ ባለሥልጣኑ አቅዶ ወደ ሥራ መግባቱን ተናግረዋል።

በ2017 በጀት ዓመት ሐምሌ እና ነሐሴ ወራትም የዘርፉ ስኬት ቀጥሏል። እሳቸው እንዳሉት፤ በእነዚህ ሁለት ወራት ብቻ 56 ሺ. ቶን ቡና በመላክ 260 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ገቢ ለማግኘት ባለሥልጣኑ አቅዶ፣ 83 ሺ. ቶን ቡና ወደ ውጭ ገበያ መላክ ችሏል፤ ከዚህም ከእቅዱ በላይ 380 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ገቢ ተገኝቷል። በተላከ ቡና መጠን ሲታይም ከእቅድ በላይ ተጨማሪ ከ30 ሺ. ቶን በላይ ቡና ወደ ውጭ ገበያ ተልኳል። በቀጣዮቹ ወራት አሁን በተመዘገበው ውጤት ልክ ማስመዝገብ ከተቻለ የበጀት ዓመቱን ዕቅድ ማሳካት እንደማይከብድም ነው ዋና ዳይሬክተሩ የገለጹት።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## የደብተር ሽፋን

**ዋስልኝ አየለ**

ትምህርት በተጀመረበት ሳምንት ከአንድ የቤተሰብ አባል ጋር ሆነን ለዘመድ ልጆች ደብተር ለመግዛት በየሱቆች ዞር ዞር እያልን ነበር። ከአንደኛው ሱቅ ገዝቶ መጣ። የደብተሮችን ሽፋን እያየን እኛ ስንማር ከነበሩት ጋር እያነፃፀርን ነበር። እሱ የሒሳብ መምህር ስለሆነ ለምዶበት ነው መሰለኝ ደብተር በትኩረት ያያል።

የዋጋው ውድነት የገበያ ሁኔታ ነውና ለመውቀስም አያስኬድም። ሲያነጋግረን የነበረው የደብተሮቹ ሽፋን ትምህርታዊ መረጃዎችን አለመያዙ ነው። ምናልባት በዚህ ዘመን የሚመረቱት ደብተሮች ሁሉ ላይሆኑ ይችላሉ፤ ዳሩ ግን እኛ ካየናቸው ቢያንስ ከአራት በላይ ሱቆች የበፊቱን አይነት ሽፋን ያለው ማግኘት ነበረብን። ምናልባት በጣም አልፎ አልፎ ከሆነ የሚገኝ ልክ አይደለም ማለት ነው።

በነገራችን ላይ ትምህርት የሚጀመረው በመስከረም ወር መጀመሪያ ቢሆንም፤ በተለይም በገጠር አካባቢ መምህርና ተማሪ ተሟልቶ መደበኛው መማር ማስተማር የሚጀመረው ግን በመስከረም ወር መጨረሻ አካባቢ ወይም በጥቅምት የመጀመሪያ ሳምንት ነው። ዋና ጉዳያችን እሱ ስላልሆነ፤ በዚሁ እግረ መንገድ ግን ስለደብተር ጀርባም እናውራ።

ተማሪነቴን ሳስታውሰው፤ መምህሩ ጠቃሚ ነገር (ሁሉም ጠቃሚ ቢሆንም የተለየ ያልኩትን) ሲናገር መሐል ላይ ካለው ዋናው ገጽ ይልቅ ከጀርባ ባለው ገጽ ላይ ነበር የምጽፈው። እንዲያውም ፈተና ላይ እንኳን የሚመጡት ከጀርባ የጻፍኳቸው ናቸው።

ቀድሞ የተማርኩባቸውን ደብተሮች እያገላበጥኩ ሳይ አሁን ካሉት ደብተሮች ጋር ብዙ ልዩነት አየሁባቸው። እንዳይገርማችሁ ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ የተማርኩበት ደብተሬ አሁን ድረስ አለ።

ደብተር በዋናነት የሚመረተው ተማሪን ታሳቢ አድርጎ ነው። ስለዚህ በደብተሩ ሽፋን ላይ የሚኖሩ ነገሮች ትልቅ ድርሻ አላቸው። ለምሳሌ ቀደም ሲል በነበሩ ደብተሮች ላይ ከፊት ለፊት ባለው ሽፋን ላይ በ2009 ዓ.ም በሞት ያጣናቸው የተረት አባት አባባ ተስፋዬ ነበሩ። አባባ ተስፋዬ ልጆች ሁሉ ሊያውቋቸው የሚገባ አባት ናቸው። ልጆችን በተረት እያስተማሩ አንጸው ያሳደጉ። እንደ እርሳቸው አይነት ታላላቅ ሰዎች መኖር ነበረባቸው።

የሚገርመው ግን በዚያው ዓመት አካባቢ ቃና ቴሌቪዥን ገና አዲስ በነበረበት በቃና ቲቪ ላይ የሚታወቁት ዛራና ቻንድራን የደብተር ሽፋን ላይ ማድረግ ተጀምሮ እንደነበር ሰምቻለሁ። የድራማውን ተወዳጅነት ማድነቅ ይቻል ይሆናል፤ ዳሩ ግን ኢትዮጵያ ውስጥ የደብተር ሽፋን የሚሆን ሰው ጠፍቶ ነው የውጭ ዝነኞች የምናደርግ? በእርግጥ በፊትም የውጭ ተጫዋቾች ፎቶ ያለበት ደብተር ነበር። የታዋቂ ሰዎችን ፎቶ እንተወውና ወደ ሳይንሳዊ መረጃዎች እንሂድ።

በመማሪያ በደብተር ላይ ሳይንስን የሚያስተምር ምልክት መኖር አለበት። ምንም እንኳን አሁን ዘመኑ የቴክኖሎጂ ስለሆነ ማንም ሰው በቀላሉ የሚያገኛቸው ቢሆኑም፤ ታሳቢ መደረግ ያለበት ግን ልጆች የስማርት ስልኮች ተጠቃሚ እንደማይሆኑ ነው።

እኔ በማስታውሰው ደብተር የፊት ሽፋን ላይ አበባ ይኖራል። የአበባ ክፍሎች ቁልጭ ብለው ይታያሉ። ተማሪዎች ደግሞ የተክሎችን አረባብ የሚማሩት በአበባ ክፍሎች ነው። ስለዚህ በቀላሉ ሁሌም በሚያዩት በደብተራቸው ላይ ሊኖር ይገባል።

በደብተሮች ላይ በዋናነት ወደታዘብኩት ነገር ስሄድ ደግሞ የደብተሩ ሽፋን ላይ ያሉ መረጃዎችን ማጣቴ ነው። አሁን ተማሪዎች የሚማሩባቸውን ብዙ ደብተሮች አየሁ። የደብተሩ ሽፋን ላይ ምንም መረጃ የለም። ልሙጥ ወረቀት ነው። ለዚያውም በጣም ስስ የሆነና በቀላሉ የሚቀደድ። የስስነቱ ነገር ዋና ትኩረቴ ባይሆን እንኳን በተማሪ ደብተር ላይ ያሉ ሳይንሳዊ መረጃዎች ለምን ቀሩ? ምናልባት ዋናው ትምህርት እንጂ በደብተሩ ላይ ያሉ መረጃዎች ተራ ነገር ይመስሉን ይሆናል፤ ግን ተራ ነገር አይደሉም። እዚያ ላይ የሚወጡ መረጃዎች ታስቦባቸው የተዘጋጁና ጠቃሚዎች ናቸው።

በተለይም ሒሳባዊ ለሆኑ ትምህርቶች ደግሞ በጣም ወሳኝ ነው። ብዙ ጊዜ የመለኪያ አሐዶች ያስፈልጋሉ። የክብደት፣ የርዝመት፣ የፈሳሽ፣ የጊዜ፣ መለኪያዎችን ከደብተር ላይ ማግኘት ለተማሪዎች ዕውቀትን ያስይዛል። ከአንዱ የመለኪያ አሃድ ወደ አንዱ ለመቀየር የግድ መታወቅ አለበት። ለምሳሌ ከኪሎሜትር ወደ ሜትር ወይም ከሜትር ወደ ኪሎ ሜትር መቀየር የሚያስፈልገው ቀመር ይኖራል። ይህን ለማወቅ አንድ ኪሎ ሜትር ስንት ሜትር እንደሆነ ማወቅ አለባቸው። ይህ ቀላል ምሳሌ ነው ያነሳሁት። በደብተር ጀርባ ላይ ከባድ ስሌት የሚጠይቁ ክፍልፋዮችም ስለሚቀመጡ በቀላሉ ለማወቅ ያግዛል።

የኬሚስትሪ ትምህርት ላይ አንድ የንጥረ ነገሮች ሰንጠረዥ አለ። ሰንጠረዡ በእያንዳንዱ ዓምድ ላይ የየራሳቸው ባሕሪ ያላቸው ንጥረ ነገሮችን ነው የያዘው። በዚህ ውስጥ የንጥረ ነገሮች ክብደት፣ የስማቸው ውክል፣ አቶማዊ ቁጥራቸው መታወቅ አለበት። ይህን የያዘ ሰንጠረዥ በቀላሉ ደብተር ላይ መገኘት አለበት። ምንም እንኳን የመማሪያ መጽሐፍ ላይ ቢኖርም ደብተር ደግሞ ከመጽሐፍ ይቀላል፤ ሁልግዜም ከተማሪው እጅ ላይ ይገኛል።

ከደብተር ጀርባ ላይ ያሉ መረጃዎች ሒሳባዊ ቀመሮች ብቻ አይደሉም። የባዮሎጂ (ሥነ ሕይወት) ትምህርትን የሚያሳዩም አሉ። ለምሳሌ የደም ዝውውር ሥርዓትን ለማሳየት፤ የደም ቧንቧዎችን ስም፣ የልብ ክፍሎችን ስም፣ ሳንባን የያዘ ምስል ከደብተር ላይ እንደነበር አስታውሳለሁ። ተማሪዎች የእያንዳንዱን የአካል ክፍል ከነስማቸው በቀላሉ ደብተር ላይ ሲያገኙት ለማስታወስ ያግዛቸዋል።

ለመሆኑ ግን እነዚህን ነገሮች በደብተር ሽፋን ላይ ማድረግ ምኑ አስቸግሮ ይሆን የተተወው? የደብተሩ ስስ መሆን ምናልባትም ለቢዝነስ ይሆናል። ምናልባት ግን የማላውቀው ሆኖ እንጂ እነዚያን ሳይንሳዊ መረጃዎች ለማስቀመጥ ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ ሆኖም ይሆናል። መቼም የደብተሩ አምራች ከዕውቀት ገንዘብ ይበልጥበታል። ግን ገዢዎች ለምን ይህን ይገዛሉ? ታዲያ ያልተመረተውን ከየት ያመጡታል? ዋናው ጥያቄ ይህ ነው!

ጉዳዩን ለወላጅም ይሁን ለአምራቹ ለሚመለከተው አካል ልተወውና በራሴ ትዝታ ነው የምሰናበታችሁ።

ያቺን ባለ 16 ቅጠል ደብተር ታውቋታላችሁ አይደል? የዛሬ ዋጋዋን ባላውቅም «የ50 ሳንቲም ደብተር» እያልን ነበር የምንጠራት። ዛሬ እኮ 20 ብር ሆና ይሆናል (ሲጀመር አለች እንዴ ግን?) ይቺን ደብተር የማስታውሳት በተለይም ከ4ኛ ክፍል በታች ነው። ደብተሯም የአንድ የትምህርት አይነት ብቻ ሳይሆን ሁሉንም ይጻፍባት ነበር። ለማባዛት የሂሳብ ስሌት ግልግል ነበረች። ከጀርባ በኩል ከ1 እስከ 12 ያሉ ቁጥሮችን ብዜትን የያዘች ነበረች። ሲጀመር ያኔ ራሴ ማባዛት ሁሉ እችል ነበር። ዛሬ ግን ሻይ ጠጥቼ እንኳን ለማስላት ስልኬን ነው የማወጣ።

ምናልባት ዘመኑ የቴክኖሎጂ ነውና ተማሪዎች እነዚያን መረጃዎች በቀላሉ ከስልካቸው ላይ ያገኙ ይሆናል። ዳሩ ግን ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በታች ያሉ ተማሪዎች ስማርት ስልክ ከሚጠቀሙ በወረቀት የተሻለ ይሆናል። በዚያ ላይ ምን ያህል ወላጅ ለልጆቹ ስማርት ስልክ መግዛት ይችላል? በሌላ በኩል ከቴክሎኖጂ ጋር እንዲተዋወቁ ቢያግዝም በልጅነት አዕምሮ ሊያቦዝናቸውም ይችላል። በደብተር እስከተማሩ ድረስ ሳይንሳዊ መረጃዎች ቢኖሩ ግን የተሻለ ነው።

# ዓለም አቀፍ



## በሰሐራ በረሃ ለ50 ዓመታት ያልታየ ዶፍ ዝናብ ዘነበ

ደቡብ ምስራቅ ሞሮኮ በሚገኘው የሰሐራ በረሃ ላይ በ50 ዓመታት ጊዜ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ዶፍ ዝናብ መጣሉን የሳተላይት ምስሎች አስመለከቱ። ለሁለት ቀናት ተከታትሎ የዘነበው ከባድ ዝናብን ተከትሎ ነው በበረሃው ውሃ መከማቸት የጀመረው። የሰሜን፣ ማዕከላዊ እና ምዕራብ አፍሪካ ሀገራትን አካልሎ የተዘረጋው የሰሐራ በረሃ በዓለማችን ረዥሙ እና ሞቃታማው በረሃ ነው።

"በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲህ ያለ ዝናብ ከጣለ ቆይቷል። ምናልባትም ከ30 እና 50 ዓመታት በፊት ነው" ሲሉ የሞሮኮ ሜቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ኃላፊ ሆሲን ዩዋቤብ ገልጸዋል። ደቡብ ምስራቅ ሞሮኮ በዓለማችን እጅግ ሞቃታማ ደረቅ ከሚባሉ ሥፍራዎች አንዱ ሲሆን ዝናብ የሚያጋጥመው በዓመታት አንድ ጊዜ ቢሆን ነው። ከሞሮኮ ዋና ከተማ ራባት 450 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው ታፎናይት በ24 ሰዓታት ውስጥ 100 ሚሊ ሊትር ዝናብ ተመዝግቧል።

የአየር ትንበያ ሙያተኞች መሰል ዝናብን 'ኤክስትራትሮፒካል ስቶርም' ሲሉ ይጠሩታል። "አየሩ በርካታ እርጥበት ሲይዝ፤ ወደላይ መትነን ይጀምራል፤ ይህ ደግሞ ዝናብ ሊያስከትል ይችላል" ሲል የሞሮኮ አየር ትንበያ ኤጀንሲ ተናግሯል። የአሜሪካው የጠፈር ምርምር ተቋም ናሳ ይፋ ያደረጋቸው ምስሎች እንደሚያሳዩት በኃይለኛው ዝናብ ምክንያት በዛጎራ እና ታታ ከተማዎች መካከል ያለው ሐይቅ ሞልቷል። ይህ ሐይቅ ላለፉት 50 ዓመታት ደርቆ ነበር የቆየው።

በዓለም ዙሪያ የዝናብ ጉዳይ እጅግ ተለዋዋጭ እየሆነ መጥቷል። "የሙቀት መጠን እየጨመረ ሲመጣ ሀይድሮሎጂካል ሳይክል የሚባለው ዑደት እየተፋጠነ ነው" ይላሉ የዓለም አየር ትንበያ ድርጅት ዋና ጸሐፊ ሴሌስት ሳውሎ። ጸሐፊዋ በሰጡት መግለጫ የዝናብ ነገር "በጣም ተለዋዋጭ እና መገመት የሚከብድ እየሆነ መጥቷል" ብለው "አሁን እየገጠመን ያለው ችግር ወይ ብዙ ዝናብ አሊያም በጣም ትንሽ እየሆነ መምጣቱ ነው" ሲሉ ያስረዳሉ።

የዓለም ሙቀት መጠን እየጨመረ በመምጣቱ አስከፊ የሚባሉ የአየር ፀባይ ለውጦች እየታዩ ነው። ሳይንቲስቶች በሚመጡት ዓመታት ተመሳሳይ ክስተት ሰሐራ በረሃ ላይ ልናይ እንችላለን ማለታቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

## ሩሲያ እና ቻይና የመከላከያ እና ወታደራዊ ግንኙነታቸውን ሊያጠናክሩ ነው

ሩሲያ እና ቻይና የመከላከያ እና ወታደራዊ ግንኙነታቸውን ለማጠናከር ያለመ ውይይት አደረጉ። ሁለቱ የእስያ ኃያላን ሩሲያ እና ቻይና ግንኙነታቸውን ለማጠናከር ያለመ የመከላከያ እና ውታደራዊ ንግግሮችን ማድረጋቸውን የሩሲያ መከላከያ ሚኒስቴር ትናንት አስታውቋል።

"ወሰን የለሽ" ያሉትን ግንኙነታቸውን እያጠናከሩ ያሉት ሞስኮ እና ቤጂንግ አሜሪካ በእስያ ተፅዕኖዋን ለማስፋት እየሠራች ነው ሲሉ ተችተዋል። የሩሲያ መከላከያ ሚኒስቴር፣ መከላከያ ሚኒስትሩን አንድሬ ቤሎሶቭን ጠቅሶ በቴሌግራም ገጹ ላይ ባወጣው መግለጫ" የሁለቱ ሀገራት ወታደራዊ ክፍሎች አንድ አይነት ዓለምአቀፋዊ ግምገማ እና በአሁናዊ ሁኔታዎች ምን መደረግ አለበት? በሚለው ጉዳይም ተመሳሳይ አረዳድ ያላቸው ናቸው" ብሏል።

ቤሎሶቭ ከቻይና ሴንትራል ሚሊታሪ ኮሚሽን ምክትል ሊቀመንበር ጋር ተገናኝተው በወሳኝ ጉዳዮች ላይ መምከራቸውን ተናግረዋል። ከስብሰባው በኋላ የቻይና መከላከያ ሚኒስቴር ሁለቱ ሀገራት ወታደራዊ ግንኙነታቸውን እንደሚያጠናክሩ እና እንደሚያስፋፉ እና በከፍተኛ ባለሥልጣናት ደረጃ ያለውን የመረጃ ልውውጥ ባለበት እንደሚያስቀጥሉ ተስፋ እንዳለው ገልጿል።

ቤሎሶቮ በቤጂንግ ጉብኝት ያደረጉት ቻይና አስፈላጊ ከሆነ በታይዋን ላይ የኃይል እርምጃ እንደምትወስድ በዛተችበት ወቅት ነው። ቻይና በታይዋን ዙሪያ 125 የጦር አውሮፕላኖችን እና የጦር መርከብ በመጠቀም ግዙፍ የተባለ የጦርነት ልምምድም አድርጋለች።

ፕሬዚዳንት ፑቲን በየካቲት 2022 በዩክሬን ልዩ ላሉት ወታደራዊ ዘመቻ ጦራቸውን ከማሰማራታቸው ከሦስት ሳምንታት ቀደም ብለው በቤጂንግ ጉብኝት ባደረጉበት ወቅት ነበር ቻይና እና ሩሲያ "ወሰን የለሽ" ግንኙነት ለማድረግ መወሰናቸውን ይፋ ያደረጉት።

እኤአ በዚህ ዓመት ባለፈው ግንቦት ወር ሁለቱ የአሜሪካ ተቀናቃኞች ፑቲን እና ሺ አዲስ የግንኙነት ምዕራፍ ለመክፈት ቃል ገብተዋል። ፑቲን እና ሺ ስትራቴጂካዊ ግንኙነታቸውን ለማጠናከር መስማማታቸውን የገለጹት ቤሎሶቭ "ውጤታማ እና ከባድ ውሳኔዎች ይጠበቃሉ" ብለዋል።

አሜሪካ ቻይና ሩሲያ በዩክሬን ለምታደርገው ጦርነት ጥቅም ላይ የሚውሉ ግብዓቶችን እያቀረበች ነው የሚል ክስ እያቀረበች ነው። ቻይና የጦር መሣሪያ ለየትኛውም አካል አለመስጠቷን እና ከሩሲያ ጋር ያላት የንግድ ግንኙነት ሊቆም ወይም ሊቋረጥ እንደማይገባ ገልጻለች ሲል የዘገበው አል ዐይን ነው።

# ስፖርት





# ኢትዮጵያ በጠረጴዛ ቴኒስ ሻምፒዮና ከ24 ዓመታት በኋላ ሜዳሊያ አስመዘገበች

ዓለማየሁ ግዛው




በአፍሪካ ጠረጴዛ ቴኒስ ሻምፒዮና ኢትዮጵያ በቡድን ወንዶች ውድድር 4ኛ ሆና በማጠናቀቅ የነሐስ ሜዳሊያ ወስዳለች፣

ኢትዮጵያ እያስተናገደች በምትገኘው የአፍሪካ ጠረጴዛ ቴኒስ ሻምፒዮና በቡድን ውድድር ከ24 ዓመታት በኋላ ሜዳሊያ ማስመዝገብ ችላለች። ከጥቅምት 2 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ ለአንድ ሳምንት በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ ጅምናዚየም የሚካሄደው የአፍሪካ አዋቂዎች ጠረጴዛ ቴኒስ ሻምፒዮና በጠንካራ ፉክክሮች ታጅቦ አምስተኛ ቀኑ ላይ ይገኛል።

በጠረጴዛ ቴኒስ ስፖርት ጠንካራ ተፎካካሪ የሆኑ ሀገራት እየተሳተፉ ሲሆን ኢትዮጵያ በሴቶች ድል አልቀናትም። በወንዶች መካከል በሚደረገው ፉክክር ግን በቡድን አራተኛ ደረጃን በመያዝ ከረጅም ዓመት በኋላ የነሐስ ሜዳሊያ ተመዝግቧል።

በሁለቱም ፆታ በተለያዩ ምድቦች ሀገራት የሚያደርጉት ፉክክር ጠንካራና በብዙ ተሰጥዖዎች የተሟላ ቢሆንም፣ ኢትዮጵያ በሜዳዋና ደጋፊዋ ፊት እንደመጫወቷ ጥሩ ተፎካካሪ ሆና ከነሐስ ሜዳሊያ በላይ ማስመዝገብ አልቻለችም። ከትናንት በስቲያ በወንዶችና ሴቶች የቡድን ምድብ የግማሽ ፍጻሜና የፍጻሜ ጨዋታዎች ሲካሄዱ፣ ሻምፒዮኑ እንዲሁም ደረጃ በመያዝ ያጠናቀቁ ሀገራት ተለይተዋል።

ይህን ታላቅ አሕጉራዊ ውድድር የምታስተናግደው ኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድኗን ከዓለም አቀፉ ፌዴሬሽን አሠልጣኝ በመጋበዝ እና በራሷ አሠልጣኞች ታግዛ ጠንካራ ዝግጅቶችን ስታደርግ ቆይታለች። ለአዘጋጅ ሀገር የሚሰጠውንም ዕድል በመጠቀምም ተጨማሪ ተጫዋቾችን ለማሰለፍ ዋናውን ጨምሮ 8 ወንዶችን እና 8 ሴት የጠረጴዛ ቴኒስ ተጫዋቾችን በማሳተፍ ላይ ትገኛለች።

በኢትዮጵያ የክለቦች ሻምፒዮና እንዲሁም ከሌሎች ሀገር አቀፍ ውድድሮች የተመረጡት ተጫዋቾችም ለዚህ ውድድር ባደረጉት ልዩና ጠንካራ ዝግጅት ጠንካራ ተፎካካሪ ሆነዋል። ውድድሮቹ በቡድን፣ በድብልቅ ፆታ፣ በጥንድና በነጠላ እየተካሄዱ ሲሆን ኢትዮጵያ ቡድንም በቡድን ውድድር በምድብ ጨዋታዎቹ ጠንካራ ሀገራትን ገጥሞ ጥሩ ተፎካካሪ በመሆን አራተኛ ደረጃን ይዞ በማጠናቀቅ ነው የነሐስ ሜዳሊያ ማግኘት የቻለችው።

በወንዶች የቡድን የምድብ ማጣሪያ ጨዋታዎች ከሱዳን እና ቱኒዚያ ጋር የተደለደለችው በሩብ ፍጻሜ ግጥሚያ ከቤኒን ተጫውታ 3 ለ 2 በመርታት ለግማሽ ፍጻሜ መድረስ ችላለች። ከምድብ ማጣሪያ ጀምሮ በቡድን ጥሩ እንቅስቃሴን በማሳየትም ለዋንጫ ለማለፍ በተካሄደው የግማሽ ፍጻሜ ፍልሚያ በናይጄሪያ 3 ለ 0 ተሸንፉ ለዋንጫ ሳታልፍ ቀርታለች። የውድድሩ ከባድ ተፎካካሪ የሆነችው ናይጄሪያ ከኢትዮጵያ በፊት በሩብ ፍጻሜው ፍልሚያ ሌላኛዋን ጠንካራ ተፎካካሪ ሀገር ቶጎን በተመሳሳይ ውጤት አሸንፋለች። በዚህም መሠረት ናይጄሪያ በቡድን ውድድር ዋንጫውን እስከማንሳት ተጉዛለች።

ናይጀሪያ በፍጻሜው ጨዋታ የሰሜን አፍሪካዋን ጠንካራ ተፎካካሪ ሀገር አልጄሪያን ገጥማም 3 ለ 1 በሆነ ውጤት በማሸነፍ ነበር በሰባት ዓመት የመጀመሪያውን የቡድን ዋንጫ ያሳካችው። በዚህ የቡድን ውድድር አልጄሪያ ሁለተኛ ሆና ስታጠናቅቅ፣ ቱኒዚያ ሦስተኛ፣ ኢትዮጵያ አራተኛ ሆና የነሐስ ሜዳሊያን ማስመዝገብ ችለዋል።

በሴቶች የቡድን ውድድር በምድብ ጨዋታዎች ኢትዮጵያ ውጤት ያልቀናት ሲሆን ግብፅ የውድድሩ አሸናፊ መሆን ችላለች። በወንዶቹ የቡድን ዋንጫ ያነሳችው ናይጄሪያ በሴቶችም የቡድን ፍልሚያ ለፍፃሜ የበቃች ቢሆንም በግብፅ 3 ለ 0 ተሸንፋለች። ግብፅ በበኩላ ለአራተኛ ተከታታይ ጊዜ ዋንጫውን ወስዳለች።

በአሕጉራዊው መድረክ ናይጄሪያና ግብፅ በውጤት ረገድ የበላይነትን የሚይዙ ሲሆን ኢትዮጵያ እአአ በ2000 እራሷ ባስተናገደችው ውድድር ሜዳሊያ ውስጥ ከገባች በኋላ ሜዳሊያ ስታስመዘግብ የአሁኑ ሁለተኛዋ ነው። ከዚህ በፊት የአዋቂዎች ጠረጴዛ ቴኒስ ሻምፒዮናን ጨምሮ በ1993 አስራ አራተኛው የመላ አፍሪካ ጠረጴዛ ቴኒስ ውድድርን እና በቅርብ ጊዜ ደግሞ የምስራቅ አፍሪካ ጠረጴዛ ቴኒስ ሻምፒዮናን በተሳካ ሁኔታ አስተናግዳለች። ውድድሩ በቀጣይ ቀናት በተለያዩ ምድቦች የማጣሪያና የፍጻሜ ፍልሚያዎችን እያስተናገደ የሚቀጥል ሲሆን፣ በመጪው ቅዳሜ አጠቃላይ አሸናፊ የሚሆነውን ሀገር በመለየት ፍጻሜውን የሚያገኝ ይሆናል።

አልጄሪያ፣ ናይጄሪያ፣ ሴኔጋል፣ ሱዳን፣ ካሜሮን፣ ጋና፣ ሩዋንዳ፣ ቱኒዚያ፣ አንጎላ፣ ቤኒን፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ቶጎ፣ ዩጋንዳ፣ አስተናጋጇ ኢትዮጵያን ጨምሮ በርካታ የአፍሪካ ሀገራት ውድድራቸውን በተለያዩ ምድቦች እያደረጉ ይገኛሉ።

ከውድድሩ መጀመር አስቀድሞ የውድድር አመራር ሥልጠና የተሰጠ ሲሆን በተጨማሪም በትናንትናው እለት የአፍሪካ ጠረጴዛ ቴኒስ ጠቅላላ ጉባኤም በአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ተካሄዷል። በመድረኩ የዓለም ጠረጴዛ ቴኒስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ፔትራ ሶርሊንግን ጨምሮ የአፍሪካ ጠረጴዛ ቴኒስ ፕሬዚዳንት፣ የኢፌዴሪ ባሕልና ስፖርት ሚኒስትር ሸዊት ሻንካ እንዲሁም የኢትዮጵያ ጠረጴዛ ቴኒስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት አቶ ተስፋዬ ብዛኔ ተብሎ ተገኝተዋል።


## የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ

በፍባለመብት እነ አቶ አብደላ ሪዲ እና በፍ/ባለዕዳ ወ/ሮ ፋጡማ ባርኬ መካከል ስላለው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በይ/መ/ቁ/ 223072 በ25/4/2016 ዓ.ም እና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 305927 በ3/11/2016 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በን/ስ/ላ ክ/ከተማ ወረዳ 2 ውስጥ በ197.37 ካ.ሜ የመሬት ይዞታ ላይ የሚገኝ መኖሪያ ቤት በካ/ቁ AA000080206149/A የተመዘገበ ካርታ ያለው የቦታው ስፋት 197,37 ካ.ሜ የሆነው የሐራጅ ሽያጭ መነሻ ዋጋ ብር 7,640,253,31 (ሰባት ሚሊዬን ስድስት መቶ አርባ ሺ ሁለት መቶ ሃምሳ ሶስት ብር ከሠላሳ አንድ ሳንቲም ) ሆኖ የትራንዛክሽን ታክስ ገዥ የሚከፍል መሆኑ ታውቆ ህዳር 9 ቀን 2017 ዓ/ም በሐራጅ ይሸጣል፡፡

የተጫራቾች ምዝገባ በ5፡00 ሰዓት ተጀምሮ የቀረቡ ተጫራቾች ተመዝግበው እንደተጠናቀቀ ወዲያዉኑ ጨረታው የሚካሄድ ይሆናል፡፡

የሐራጁ ሽያጭ የሚካሄደው በፌደራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት የጨረታ አዳራሽ ውስጥ ሲሆን፣ ንብረቱን ተጫርተው ለመግዛት የሚፈልጉ ተጫራቾች ከጨረታው ቀደም ብሎ ባሉት አራት የሥራ ቀናቶች ውስጥ ባለመብቱ ለማስጎብኘት በሚመርጧቸው ሶስት የስራ ቀናት በፌ/ፍ/ቤቶች ፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ሐራጅ ክፍል ድረስ ከጠዋቱ በ3፡30 ጀምሮ በመገኘትና ባለመብቱ በሚያቀርበው ትራንስፓርት ንብረቱን ባለበት ቦታ ድረስ በመውሰድ መጎብኘት የሚችሉ ሲሆን እያንዳንዱ ተጫራች በሚጫረትበት ወቅት የንብረቱን ግምት 1/4ኛውን በንግድ ባንክ በተረጋገጠ C.P.O ማስያዝ ይኖርበታል። ከ1/4ኛ አስበልጦም ሆነ አሳንሶ CPO የሚመጣ ተጫራች በጨረታው አይካፈልም። በጨረታው አሸናፊ የሆነው ግለሰብ አሸናፊ የሆነበትን ገንዘብ በአጠቃላይ ጨረታውን ከአሸነፈበት ቀን ጀምሮ በፍ/አ/ዳ/ስም C.P.O አሰርተው በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በተከፈተ አካውንት አሰርቶ መሉ ገንዘቡን በ15 ቀናት ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት የፍ/አ/ዳይሬክቶሬት ንብረቱን በህጋዊ መንገድ በሀራጅ ስለመሸጡ ለሚመለከተው አካል ማስረጃ ከመፃፍ ባለፈ ስም የማዛወር ግዴታ የሌለበት መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት**

## የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ

በፍ/ባለመብት ወ/ሮ አዚዛ ሰኢድ እና የፍ/ባለዕዳ አቶ ኑርሁሴን ሀሰን መካከል ስላለው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር/106623 በ7/8/2014 ዓ/ም እና በኮ/መ/ቁ/130350 በ27/10/2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በልደታ ክ/ከተማ ወረዳ 7 ወስጥ የሚገኝ የህንፃ ቁጥር ብሎክ 4 የቤት ቁጥር 06 የሆነው ኮንዶሚኒዬም ቤት የሐራጅ መነሻ ዋጋ ብር 3,531,273 (ሦስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሰላሳ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ሰባ ሦስት ብር) ስፋቱ 48.79 ካ/ሜ በመለያ ቁጥር AA00030700062 የተመዘገበ ካርታ ያለው ሆኖ የትራዛክሽን ታክስ ገዥ የሚከፍል መሆኑ ታውቆ ህዳር 11 ቀን 2017 ዓ/ም በሐራጅ ይሸጣል፡፡ የተጫራቾች ምዝገባ 5፡30 ሰዓት ተጀምሮ የቀረቡ ተጫራቾች ተመዝግበው እንደተጠናቀቀ ወዲያዉኑ ጨረታው የሚካሄድ ይሆናል፡፡

የሐራጁ ሽያጭ የሚካሄደው በፌደራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት የጨረታ አዳራሽ ውስጥ ሲሆን፣ ንብረቱን ተጫርተው ለመግዛት የሚፈልጉ ተጫራቾች ከጨረታው ቀደም ብሎ ባሉት አራት የሥራ ቀናቶች ውስጥ ባለመብቱ ለማስጎብኘት በሚመርጧቸው ሶስት የስራ ቀናት በፌ/ፍ/ቤቶች ፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ሐራጅ ክፍል ድረስ ከጠዋቱ በ3፡30 ብቻ በመገኘትና ባለመብቱ በሚያቀርበው ትራንስፓርት ንብረቱን ባለበት ቦታ ድረስ በመውሰድ ለመጐብኘት የሚችሉ ሲሆን እያንዳንዱ ተጫራች በሚጫረትበት ወቅት የንብረቱን መነሻ ግምት 1/4 ኛውን በንግድ ባንክ በተረጋገጠ C.P.O ማስያዝ ይኖርበታል፡፡ ከ1/4ኛው አስበልጦም ሆነ አሳንሶ የሚመጣ ተጫራች በጨረታው አይካፈልም። በጨረታው አሸናፊ የሆነው ግለሰብ አሸናፊ የሆነበትን ገንዘብ በአጠቃላይ ጨረታውን ከአሸነፈበት ቀን ጀምሮ በፍ/አፈ/ዳ/ ስም C.P.O አሰርቶ በኢትዮያ ንግድ ባንክ ብቻ ሙሉ ገንዘቡን በ15 ቀናት ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡ የፍ/አፈ/ዳይሬክቶሬት ንብረቱን በህጋዊ መንገድ በሐራጅ ስለመሸጡ ለሚመለከተው አካል ማስረጃ ከመጻፍ ባለፈ ስም የማዛወር ግዴታ የሌለበት መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት**